## ዓለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይዝ ማዕከል (CIPE)

# ውጤታማ የሆነ የአድቮኬሲ ሥራን እንዴት ማከናወን ይቻላል?

## ለንግድ ማኅበራት የተዘጋጀ መመሪያ

ጃንወሪ 2003

የአሜሪካ ንግድ ምክር ቤት ዘርፍ

ማውጫ

**ክፍል አንድ :መግቢያ ........................................................................................................ 4**

**ክፍል ሁለት :አድቮኬሲ ምንድነው?.......................................................................................... 4**

**ክፍል ሦስት :ፖሊሲ ላይ አድቮከሲ መሥራት ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው?..................... 7**

**ክፍል አራት የተዋጣለት የአድቮኬሲ እቅድ እንዴት ማዘጋጀትና መተግበር ይቻላል?............... 9**

**ክፍል አምስት- አባሪ ሰነዶች**

**አባሪ ሀ- የአሜሪካን ንግድ ምክር ቤት ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ቀዳሚ ጉዳዮች ጥናት መጠይቅ (2003-2004) ........................................................................................ 40**

**አባሪ ለ - በምስራቅ አውሮፓ ማሻሻያን ለማበረታታት ቅንጅትን ስለመፍጠር ............ 44**

**አባሪ ሐ - በዓለም ዙሪያ ውጤታማ የሆኑ የቢዝነስ አጀንዳዎች .................................. 45**

**አባሪ መ - በዓለም አቀፍ ደረጃ የሕግ አማካሪነት መርሀ ግብሮች .............................. 49**

የግል ኢንተርፕራይስ ዓለም አቀፍ ማዕከል (CIPE) ) ተልእኮ የግል ንግድ ድርጅቶችን እና ገበያ መር የኢኮኖሚ ማሻሻያን በማስፋፋት በመላው ዓለም ዲሞክራሲን መገንባት ነው፡፡ የአሜሪካን ንግድ ምክር ቤት አንድ አካል በመሆን እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1983 የተመሰረተው ሳይፕ በመሠረቱ ድጋፍ የሚያገኘው ናሽናል ኢንደውሜንት ፎር ዲሞክራሲ ሲሆን፣ ተጨማሪ ድጋፎችንም ከግል ተቋማትና ከአሜሪካን ዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት ያገኛል፡፡ ሳይፕ በ20 ዓመት ዕድሜው ከፖሊሲ አውጪዎች፣ ከንግድ መሪዎችና ከጋዜጠኞች ጋር በመሆን 80 በሚደርሱ ሀገራት 700 የሚደርሱ ፕሮጀክቶችን በመዘርጋት ለዲሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ወሳኝ የሆኑ የሲቪክ ተቋማትን በመገንባት ሠርቷል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ የድርጅቱን ድረ- ገጽ www.cipe org መጐብኘት ይቻላል፡፡

ይኼንን ህትመት አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ የምርምርና አድቮኬሲ ፕሮግራም ኦፊሰር ከሆኑት ካተህራይን ኤል ኩቺታ ሄልብለንግ እና ከኤዝኪዩቲቭ ዳይሬክተር ጆህን፣ዲ ሱሊቫን ማግኘት ይቻላል፡፡


አድራሻ

የግል ኢንተርፕራይስ ዓለም አቀፍ ማዕከል

1555 15 ኛ መንገድ ኤን ደብሊው ሱዊት 700፣ ዋሽንግተን ዲሲ 2005 ዩ.ኤስ.ኤ

ስልክ (202)721-9200

ፋክስ (202)721-9250

ድረ-ገጽ **www.cipe.org**

# ክፍል አንድ፡ መግቢያ

በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገራት የታየው ተሞክሮ እንደሚያሳው የኢኮኖሚ ማሻሻያ እውነተኛ ውጤት ሊያስመዘግብ የሚችለው የንግድ ማኅበራት የአድቮከሲ ሥራን በመሥራት ድምጻቸውን ማሰማት ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ የንግዱ ማኅበረሰብ በኅብረተሰቡ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብና ለዚሁም የሥራ እድል በመፍጠር የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት የሚያፋጥን አካል በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በፖሊሲ ቀረጻ ሂደት ውስጥ ተደማጭነት ሊኖረው ይገባል፡፡ የንግድ ማኅበራት ትምህርትንና የሥራ ፈጠራ ሥልጠናን እንደሚያካሂዱና እንደሚሰጡም ማጤን ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ሥራ ፈጠራን ወይንም ኢንተርፕረነርሺፕን ለማሳደግ ያለው የቢዝነስ ሁኔታ አመቺ ካልሆነ ይህ ሁሉ ጥረት ፍሬ አልባ ነው የሚሆነው፡፡ ውጤታማ የሆኑ የንግድ ማኅበራት የአባላቶቻቸውን ጥቅም በሚነኩ ፖሊሲዎች ዙሪያ የትምህርት ዓላማቸውንና የአድቮከሲ ፕሮግራማቸውን በማቀናጀት ነው የሚሠሩት፡፡ ዓለም አቀፍ ውድድር በደራበትና ነጋዴዎች የንግድ ማኅበራትን በሚፈልጉበት በአሁኑ ወቅት የአድቮከሲን ሥራ ችላ የሚል የንግድ ማኅበር ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በእርግጥም የአድቮከሲ ሥራን በማከናወን ችግር ያለባቸውን ፖሊሲዎች እንዲስተካከሉ ማድረግ ለማኅበራት ስኬትና በሕይወት መቆየት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት፡ አድቮከሲ ምንድን ነው?

በቀላል አገላለጽ አድቮከሲ ማለት በአንድ የተወሰነ ነጥብ ዙሪያ ወይንም በአንድ ወገን ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ወይንም ለመደገፍ መንቀሳቀስ ማለት ነው፡፡ የመንግሥት ፖሊሲ አድቮከሲ የሚባለው አንድን የተወሰነ የመንግስት ፖሊሲ በማስለወጥ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህም፡-

- ህግንና ሌሎች ህግ ነክ ጉዳዮችን
- ደንቦችን
- የችሎት ውሳኔዎችን
- የኤስኪዩቲቭ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን
- የፖለቲካ ፓርቲዎች መመሪያዎችን
- የልዩ ልዩ ተቋማት ፖሊሲዎችን ያጠቃልላል፡፡

በሌላ አገላለጽ፣ በመንግሥት ፖሊሲ ላይ የሚሠራው አድቮከሲ በአንድ በተወሰነ ለንግዱ ኅብረተሰብ አሠራር ተስማሚነት በሌለው የመንግሥት ፖሊሲ ላይ ድምጽን በማሰማትና ለዚያም የተሰባሰበ ድጋፍ ለመስጠት አቋም መውሰድ ላይ ያተኮረ ነው:: የሚወሰደው አቋም የተጠቀሰውን ፖሊሲ ማጽደቅን ፣ ማሰረዝን፣ ውድቅ ማድረግን እና በዚያው ላይ ተጨማሪ ማድረግን ያካተተ ነው:: በተለይ በመንግሥት ፖሊሲ ላይ የሚሠራው አድቮከሲ በተወሰኑ መልኩ የመንግሥትን አቋም እስከመቃወም የሚደርስ በመሆኑ አስቸጋሪነት ሊኖረው ይችላል::

አብዛኛዎቹ የመንግሥት ፖሊሲዎች በቀጥታ የንግድ እንቅስቃሴዎችን የሚነኩ በመሆናቸው የግድ የግል ዘርፉን ድምጽ ማሰማት የሚፈልጉ ናቸው:: እነዚህ ላይ መሥራት ደግሞ በርካታ የመንግሥት ፖሊሲዎች እንዲሻሻሉ ለማድረግ ይረዳል::

ይህም:-

. ከንግድ

. ከሠራተኛ

.ከደህንነት

.ከትራንስፖርት

.ከፋይናንስ

.ከታክስ

.ከታሪፍ እና

.ከሌሎች ከንግድ ሥራ ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን የተመለከቱ ሕጐችና ደንቦችን የሚያካትት ነው::

ይህ ከሆነ በርካታ በዚህ ዙሪያ ያሉ ነጋዴዎች በግሉ የዘርፍ የማኅበራት አማካኝነት በአንድ በተወሰነ ነጥብ ላይ በክፍለ ከተማ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ በቋሚነት አቋማቸውን ማሳወቅ ይችላሉ:: ለንግድ ማኅበራት አባሎቻቸውን ስለመንግሥት ፖሊሲ ማስተማርና በፖሊሲዎች ላይ ያላቸውን ቅሬታ አሰባስቦ ወደ አንድ ድምጽ ማምጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ይህም አንድ የተወሰነ ፖሊሲ የሚያስከትለውን ወይንም ያለውን ጉዳትና ጥቅም ለይቶ ለማውጣት ይረዳል:: በዚህ መልክ መደራጀት ደግሞ መንግሥት በሚያወጣቸው ለንግዱ ኅብረተሰብ ተስማሚ ያልሆኑ ፖሊሲዎች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ የሚያስችል ነው:: በአጠቃላይ ይህ የሚደረገው ወይንም ይህ ጥረት ዓላማ የሚያደርገው መልካምና የተስተካከለ የንግድ እንቅስቃሴን መመስረትና ማጐልበት ላይ ነው::

የንግድ ማኅበራቱ የአድቮኬሲ የሚሳተፉት በግዴታ ወይንስ ሙሉ በሙሉ በበጐ ፈቃደኝነት ነው? በሚለው ላይ የተመሠረተ ነው::

## *የመንግስት ፖሊሲ ላይ የሚሠራ አድቮከሲ የሚያካትታቸው፤*

*በመንግስት ፖሊሲ ላይ የሚሠራውን አድቮከሲ ማወቅ ተገቢ የሆነውን ያህል በዚሁ ዙሪያ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችንም ጠንቅቆ ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው:: ከንግድ ማኅበራት አመለካከት አኳያ የመንግሥት ፖሊሲ ላይ የአድቮከሲ ሥራ መሥራት ማለት አባላቶቻቸው የንግድ እንቅስቃሴያቸውን በተሳካና በተቃና መልኩ እንዲያከናውኑ ከማስቻል አንጻር ብቻ የታቀደ ነው እንጂ ከዚህ በሚከተለው ዓይነት አይታቀድም::*

*- ለአንዱ የንግድ ዘርፍ የተለየ እና አድሎአዊ ጥቅም ለማስገኘት፣*

*- የአባላት የእለት ከእለት የንግድ እንቅስቃሴ ላይ የተፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት፣*

*/ይሁን እንጂ በየቀኑ በንግድ ሥራ ላይ የሚፈጠሩ መሰናክሎች በአጠቃላይ በንግዱ ኅብረተሰብ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች እንዳሉ አመላካቾች ናቸው:: የዚያን ጊዜ የመንግሥት ፖሊሲ ላይ የሚሠራ የአድቮከሲ ሥራን ማካሄድ ይቻላል:: በዚህን ወቅት ግን ችግርን ለማስወገድና ለመፍታት ቀድሞ የችግሩን እውነተኛ ምክንያት ማወቅ ያስፈልጋል::/*

*- ከዘወትር የግብይት ወይንም በአባላትና በመንግሥት መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባት ከመቅረፍ ጋር የተያያዙ የእለት ከእለት ችግሮችን የመፍታት አገልግሎቶችን ለአባላት መስጠት:: የዚህ ዓይነት ችግሮች በአባላት ላይ ሲከሰቱ አባላት የሕግ ባለሙያዎችን፣ በዚህ ዙሪያ ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን፣ አማካሪዎችንና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን መጠቀም ይችላሉ::*

ከአባላቶቻቸው በግዴታ ላይ የተመሠረተ የአባልነት ክፍያ የሚሰበስቡና መንግሥት በዚህ መልክ የሚደጉማቸው ማኅበራት በዚህ ዓይነት የአድቮከሲ ሥራ ላይ ሲሰማሩ በሚያካሂዷቸው የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ላይ እገዳ ሊጣልባቸው ወይንም የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል:: ስለዚህ ይህ የአድቮከሲ መመሪያ በተለይ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአባልነት መዋጮ ያላቸው የግል ዘርፍ ማኅበራት እንዴት የአድቮኬሲ ሥራን ማዘጋጀትና መተግበር እንደሚችሉ ለማሳየት የተዘጋጀ ነው::

# ክፍል ሦስት፡ ፖሊሲ ላይ አድቮከሲ መሥራት ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው?

## የንግድ ዘርፉን ድምጽ ተደማጭ ማድረግ

ውጤታማ የሆነ የአድቮከሲ ሥራ በመንግሥት ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ ማሳደር ለሚችሉ አካላት ወሳኝ ነው፡፡ በፖሊሲው ላይ ተጽዕኖ ያላቸውን መረጃዎችንም በስፋት ያቀርባል፡፡ አካላት የሚባሉትም የሚከተሉት ናቸው፡-

. ***መገናኛ ብዙሃን፡*** በዚህ ውስጥ የሚካተቱት ከንግድ ማኅበራት ከፍተኛ ጥቅም የሚያገኙና ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶችንና ትችቶችን የሚያሰፍሩ ናቸው፡፡

. ***ሕግ አውጪዎች፡*** የተሠራው የአድቮከሲ ሥራ መረጃ ለህግ አውጪዎች እንዲደርሳቸው የሚደረገው ማህበራት በፖሊሲ ላይ የሚሰጡት ውሳኔ የመረጣቸውን ሕዝብ ህይወት ሊጐዳ ስለሚችል ነው፡፡ የመረጣቸው ሕዝብ ደግሞ በእነዚህ ሰዎች ድጋሚ መመረጥና አለመመረጥ ላይ ከፍተኛ ሚና ያለው ነው፡፡ የተዋጣለት ፖሊሲ ለቢዝነስ የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል የተሻለ ገበያ ቀመስ ማሻሻያን በማስገኘት በአጠቃላይ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ መልካምና የተሳካ የቢዝነስ እንቅስቃሴ መኖር አንቨስትመንትን ለመሳብና ሥራ ፈጣሪነትን ለማበረታታት የሚረዳ ሲሆን፤ ይህም የኢኮኖሚ እድገትን የሚያነሳሳና ጥሩ ክፍያ የሚያስገኙ ጥራት ያላቸውን የሥራ መስኮች የሚከፍት ነው፡፡ መላው የሀገሪቱ ዜጋም በዚህ አዲስ እድል ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

. ***ሕግ አስፈፃሚዎች፣ ሲቪል የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና አስተዳደሪዎች፡*** እነዚህ አካላት ጫና እየፈጠረ በሚገኝ በአንድ በተወሰነ ፖሊሲና ደንብ ላይ መረጃ እንዲኖራቸው ከተደረገ ራሳቸውን እንዲያጠናክሩ እና የሥራ አፈጻጸማቸውንም በተሳካ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ይረዳቸዋል፡፡

. ***በአጠቃላይ ሕዝቡ፡*** የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት አባላትን ጨምሮ እነዚህ አካላት በሕግ አወጣጥ ውሳኔዎች ላይ ጫና መፍጠር የሚችሉ ናቸው፡፡ ሕዝቡና የንግድና የዘርፍ ማኅበራት አባላት ችግር ባለባቸው ፖሊሲዎች ላይ ቁልፍ መረጃ ሲኖራቸውና በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሲደረግ የመረጧቸው ተወካዮች እነርሱን ወክለው ተቀምጠው ምን እያደረጉ እንደሚገኙና ምንስ በትክክል ለመፈፀም እንዳልቻሉ ለማወቅ ይረዳቸዋል፡፡ የዚያን ጊዜ ሕዝቡና የንግድና የዘርፍ ማኅበራት እንደነዚህ ዓይነት የህዝብ ተወካዮች ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

## የንግድ ማኅበራት ማጠናከር

አድቮኬሲ አንድ የቢዝነስ ማህበር በህይወት እንዲኖርና ያላሰለሰ እድገት እንዲደረግ ይረዳል፡፡ የቢዝነስ ማህበራት አላማ አባሎቻቸውን ማገልገል ነው፡፡ ይህንም ለማድረግ አያሌ የቢዝነስ ትምህርትና ስልጠናን የመሳሰሉ ግልጋሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ ሆኖም ውጤታማ ኢንተርፐሬነር ለመሆን የሚያስችሉ ህጎችና የቁጥጥር መመሪያዎች ባሉበት ሁኔታ እነዚህን ግልጋሎቶች ለማበርከት የሚደረግ ጥረት ሁሉ ከንቱ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔዎች ባሉበት ወቅት እንቅፋቶቹን በማስወገድ የማህበራት አባላትን የንግድ እንቅስቃሴዎች ቀጣይና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማገዝ የአድቮኬሲ ስራ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## የተዋጣለት የአድቮኬሲ ሥራን የሚሠሩ ንግድ ማኅበራት መገለጫ ባሕርያት

የተዋጣለት የአድቨኬሲ ሥራን የሚሠሩ የንግድ ማኅበራት ከዚህ በሚከተሉት ባሕሪያት የሚታወቁ ናቸው፡፡

- የአባላቶቻቸውን ጉዳይ በጠራ ሁኔታ ለይተው በማውጣት የተባበረ እና ወጥ ድምጽ እንዲኖረው በማድረግ የሕግ አውጪዎችን ትኩረት በፍጥነት ይስባሉ፣
- ከወሳኔ ሰጪ አካላት ጋር በቁልፍ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ለመወያየትና በዚያ ዙሪያ የተሠሩ ወሳኝ የጥናት ሕትመቶችን ለማቅረብ በመደበኛነት ይገናኛሉ፣
- ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር መደበኛ የግንኙነት መስመርንና መልካም የሥራ ግንኙነት ይፈጥራሉ፣
- ይኼንኑም የግንኙነት መስመር በመጠቀም የአባላቶቻቸውን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር ሊተገበሩ እየተዘጋጁ ባሉ ሕጎችና ፖሊሲዎች ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ ከሁሉም በላይ ይህ በመደረጉ ፖሊሲ አውጪዎች የንግድ ማኅበራትን ፖሊሲ በማውጣት ሂደት ውስጥ እንደ ቁልፍ ተሳታፊና ከፖሊሲው ጋር በተያያዘም ማኅበራትን ጠቃሚ መረጃን እንደሚሰጡ አካላት አድርገው እንዲቆጥሯቸው ያደርጋል፡፡ በአንዳንድ ሀገራት በሳይፕ ለሚታገዙ የንግድ ማኅበራት የአድቨኬሲ ፕሮጀክቶች ምስጋና ይግባቸውና ፖሊሲ አውጪዎች ከፖሊሲ ጋር የተያያዙ ምክሮችን ለማግኘት ሙሉ በሙሉ ፊታቸውን ወደ ንግድ ማኅበራት እንዲያዞሩ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- ከአባላቶቻቸው ጥቅም ጋር በተያያዘ ሊወጡ በተዘጋጁ ወይንም በወጡ ፖሊሲዎች ላይ የአድቮኬሲ ሥራን ይሠራሉ፡፡ የንግድ ማኅበራት ተወካዮች ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር በመደበኛ ሁኔታ በመገናኘት የፖሊሲው አጀንዳ የነርሱን ጉዳይ እንዲያካትት በማስቻል በሌሎች ውስን ፖሊሲዎች ላይ ደግሞ ለእነርሱ የሚስማሟቸውን መነሻ ሐሳቦች ያቀርባሉ፡፡

- የውጭ ባለሀብቶችን የሚያስጉና ለሥራ ፈጣሪዎች እንቅፋት የሆኑ ተደጋጋሚ ለውጦች የሚታዩባቸውን ከቢዝነስ ጋር የተያያዙ ሕግ ነክና የቁጥጥር ማዕቀፎችን በመከላከል ረገድ እርዳታ ያደርጋሉ፡፡
- የአባላቶቻቸውን ጥቅም ከማስጠበቅ እና ከማረጋገጥ አኳያ የፖሊሲ አስተዳደርና አተገባበር በተገቢ ሁኔታ የማስተዳደር ሥራ እየተሠራበት መሆኑን፣ ወጥነት ያለው መሆኑን እና በፍጥነት መካሄዱን ይቆጣጠራሉ፣ ይህን በማድረጋቸውም የህግ የበላይነትን ያጠናክራሉ፡፡

የንግድ ማኅበራት የአድቮከሲ ሥራን በመስራት በፖሊሲ ማውጣት ዙሪያ ዋና ተሳታፊ ሊሆኑና ራሳቸውንም ሊያጠናክሩ ይችላሉ፡፡ የተዋጣለት የአድቮከሲ ሥራን መሥራት የማኅበራቱን ደረጃ በፖሊሲ አውጪዎች ዘንድ ከፍ አድርጐ የሚያሳይ ሲሆን፣ በንግድ ኅብረተሰቡ ዘንድም ማህበሩ ለአባላቱ ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት እንደሚሰጥ በተግባር የሚያሳይና ክብሩንም የሚያጐላ ነው፡፡ ይህም የቋሚ አባላትን መዋጮና ድጋፍ የሚያሳድግ ሲሆን፣ አዳዲስ አባላትንም ለመሳብ ይረዳል፡፡ የንግድ ማኅበራት በቂ በጀት መድበው ኃይላቸውን በማጠናከር የአድቮከሲ ሥራ መሥራት የሚችሉ ሲሆን፣ ይህን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወንም የአድቮከሲ ስልትና እቅድን መንደፍ ያሻቸዋል፡፡ ለማኅበራት አባለቶቻቸውን ማብዛት ማለት በምርጫ ወቅት አንድ ዓይነት ሐሳብ ያላቸውን የአንድ አካባቢ ድምጽ ሰጪዎችን እንደማሰባሰብ ነው፡፡ ይህም በሕዝብ ድምጽ ተጽእኖ ስር የሚሆኑ ፖሊሲ አውጪዎችን ያስገኛል፡፡ ባጭሩ የአድቮከሲ ሥራ የንግድ ማኅበራት አባላት አስፈላጊ መረጃዎች እና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ የንግድ ሥራቸውን እንዲጠብቁና እንዲያሳድጉ የሚረዳቸውን መሣሪያ የሚያስታጥቃቸው ሲሆን፣ በዚሁም ማኅበራቱ ለአባላቶቻቸው የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲያሳድጉ የሚያደርግ ነው፡፡

# ክፍል አራት፡ የተዋጣለትን የአድቮኬሲ እቅድ እንዴት ማዘጋጀትና መተግበር እንደሚቻል?

## ተግባር አንድ፡ የአድቮኬሲ ኮሚቴን ማቋቋም

በአድቮከሲ ሥራ ለመሳተፍ የሚፈለጉ የንግድ ማኅበራት የሚቻላቸው ከሆነ በዋናነት አድቮከሲ የሚሠራ የአድቮከሲ ኮሚቴ ማቋቋም አለባቸው፡፡ ኮሚቴው በመጠኑ አነስ ብሎ ከአምስት እስከ ሰባት አባላት ኖሮት፣ አባላቱም የማኅበሩን የተለያዩ ዘርፎች የሚወክሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ማኅበሩ በተለያዩ እንዱስትሪዎች ውስጥ የሚካተቱ አነስተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ የንግድ ድርጅቶችን የሚወክል ከሆነ የሚቋቋመው ኮሚቴም ከሁሉም አይነት የንግድ

ድርጅቶችና ከተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የሚወከሉ አባላት ሊኖሩት ይገባል፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ሁሉንም ዘርፎች ሊወክሉ የሚችሉ ግለሰቦችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

የኮሚቴው አባላት እያንዳንዱን ዘርፍ ከመወከላቸው በላይ ግን የማኅበራቸው አባላት ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ከፖሊሲ ጋር የተያያዙ ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ እነዚህ የኮሚቴ አባላት በራሳቸው ንግድ ዙሪያ ያሉ የፖሊሲ ችግሮችን ሳይሆን የመላውን የማኅበሩን አባላት ችግሮች እንደሚያነሱ ሊግባቡ ይገባል፡፡ የአድቮከሲ ሥራውን ለመሥራት የሚቋቋመው ኮሚቴ አባላት ለዚህ ተግባር በቂ የሆነ የሥራ ጊዜያቸውን በመደበኛነት ለመመደብ ፍቃደኛነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህም፡-

. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ በመገኘት፣

. የአድቮኬሲ ስራውን ለመሥራት የሚደረገውን ጥረት ቅርጽ በማስያዝና በመከታተል፣

. የተዘጋጁ የእቅድ ሰነዶችን በማንበብ፣ የአርትኦት ሥራ በመሥራትና በማጽደቅ እንዲሁም

. አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የማኅበሩን አባላትና ፖሊሲ አውጪዎችን ማግኘትንና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

ኮሚቴው ሰብሳቢ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህም ሰብሳቢ የኮሚቴው እንቅስቃሴዎች በተገቢው ሁኔታ እየተካሄዱ መሆናቸውንና የኮሚቴው ዓላማዎች ግብ መድረሳቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ የኮሚቴው ሰብሳቢ የዚያ ኮሚቴ አባል ለመሆን የሚያስፈልጉት ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች እንዳሉ ሆነው ከዚህ በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ብቃት ሊኖረው ይገባል፡፡

. በቡድን አንድ ሆኖ የመሥራትና የሥራ ቡድንንም የመምራት የተረጋገጠ ችሎታ፣

. ፖሊሲ የሚቀረጽበትን ዝርዝር ሁኔታ ጠንቅቆ የመረዳት ብቃት፣

. አግባብነት ካላቸው ፖሊሲ አውጪዎች ጋር አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት፡፡

እነዚህን ተግባራት ለማከናወንና የኮሚቴውንም ሥራዎች በቂ ስልት አውጥቶ ለመሥራት እንዲችል የአድቮከሲ ኮሚቴ ሰብሳቢው የዋናው ማኅበር ሊቀመንበር መሆን የለበትም፡፡ ይህ ከሆነ የኮሚቴው ሰብሳቢ ከማኅበሩ ሊቀመንበር፣ ከሌሎቹ የኮሚቴ አባላትና ከመላው የማኅበሩ አባላት ጋር ጥሩ የሥራ ግንኙነት ለመፍጠር ይችላል፡፡

የአድቮከሲ ሥራን የሚሠራው ኮሚቴ ተልእኮውን ውጤታማ በሆነ መልኩና በወቅቱ ለማከናወን እንዲችል ከተቻለ የራሱ የሆነ በጀትና ለዚህ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ሊኖሩት ይገባል፡፡ በጀት ከተመደበ የኮሚቴው ሰብሳቢ በመጪዎቹ አንድ ወይንም ሁለት ዓመታት ሊሰሩ ለታቀዱ ተግባራት አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ከወዲሁ በዝርዝር ማዘጋጀት ይችላል፡፡ የማኅበሩ በጀት የሚወስነው ምን ያክል ቅጥር ሠራተኞችና አማካሪዎች ከውጪ

ይቀጠሩ?፣ የማኅበሩ አባላት የሆኑ ድርጅቶችስ ለዚህ ኮሚቴ ምን ያክል አገልግሎት እና እገዛ ይስጡ የሚሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል፡፡

የአድቮከሲ ኮሚቴው ሠራተኞች ሊኖራቸው የሚገባቸው ክህሎቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

. ከማኅበራት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የዳበረ የምርምር ክህሎት፣

. የጐለበተ የመገናኛ ብዙሃንና የሕዝብ ግንኙነት ክህሎት፣

. ቅንጅት የመፍጠር ችሎታ፣

. የማርኬቲንግ እውቀት፣

. ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር ጥሩ ትስስር የመፍጠርና ከፖሊሲ አውጪዎች ባልደረቦች ጋርም በትብብር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት የመፍጠር ችሎታ መኖር፡፡

የአድቮከሲ ኮሚቴው አባላት ኮሚቴውን መርዳት በሚያስፈልግበት ሰዓት የራሳቸውን ድርጅት ሠራተኞች ለኮሚቴ ሥራ መጠቀም እንደሚገባ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ኮሚቴው ከዚህም በተጨማሪ ምናልባትም የሕግ ወይንም የአድቮኬሲ ኤክስፐርቶችን ቁልፍ የሆኑ አዋጆችን እንዲያረቁ ወይንም የተወሰነ ጠቃሚ ጉዳይን እንዲከታተሉ ለማድረግ ሊቀጥር ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነት ባለሙያዎች እንደአስፈላጊነቱ በኮንትራት ወይንም በትርፍ ሰዓት ሥራ ሊቀጠሩ ይችላሉ፡፡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መልካም ግንኙነት ያላቸው በርካታ የቀድሞ የፓርላማ አባላትና በጡረታ ላይ የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎችም የዚህን ዓይነት ሥራ በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሥራት ፍቃደኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የተወሰኑ የአድቮኬሲ ኮሚቴ ሠራተኞች ልዩ የእንባ ጠባቂ ሚና እንዲኖራቸው ተደርጐ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ሲደረግ እነዚህ ሠራተኞች በሂደት ላይ የሚገኙ አንዳንድ ከአድቮከሲ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በንቃት የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት ለተወሰነ ሰው ተሰጠ ማለት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ተግባር ከማኅበሩ እንቅስቃሴ በተቃራኒ የሚገኙትን ፖሊሲ አውጪዎች፣ የህብረተሰብ ክፍሎች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማኅበሩ የሚያከናውናቸው የአድቮከሲ ሥራዎችን አስመልክቶ ምን እያወሩና ምን እያደረጉ እንደሚገኙ በአፍላው ለማወቅ ይረዳል፡፡ ይህንን ማድረግ ደግሞ ፖሊሲ ላይ የሚደረገውን ውይይት ቅርጽ ለማስያዝ ያግዛል፡፡ ማኅበራት ፖሊሲ ላይ ጫና የማሳደር እድል የሚኖራቸው ፖሊሲው ከፀደቀና መስመር ከያዘ በኋላ ሳይሆን ከመጽደቁ በፊት ነው፡፡ ምክንያቱም ፖሊሲው አንዴ ከፀደቀ በኋላ የፖሊሲው ደጋፊዎች ፖሊሲውን በቀላሉ ሊከላከሉት ስለሚችሉ ነው፡፡

የአድቮከሲ ኮሚቴው አንዴ ከተቋቋመና ሠራተኞቹም ከተቀጠሩ በኋላ፣ የኮሚቴው ሰብሳቢ ከኮሚቴው አባላትና ከሠራተኞች ጋር በመመካከር ጊዜያዊ የስብሰባ መርሃ ግብር ማውጣት አለበት፡፡ መደበኛ የስብሰባ ጊዜ መኖር ውጤታማ የትብብር መንፈስን ለማዳበርና አስፈላጊ ሲሆንም ችግሮችን ለመፍታት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ የኮሚቴው ሰብሳቢ ለምሳሌ

ዘወትር ማክሰኞ ጠዋት በ3፡00 ሰዓትና የመሳሰሉ ሰዓቶችን በቋሚነት የሰብሰባ ጊዜ አድርጐ ቢመድብ የሚመከር ነው፡፡ ይህን በማድረጉም የኮሚቴው አባላት ያንን ሰዓት በቋሚነት ከሌላ ሥራ ነፃ አድርገው ለኮሜቴው ስብሰባ እንዲመድቡት ይረዳቸዋል፡፡ የስብሰባው ጊዜ ብዛት በሚከናወኑ ተግባራት ላይ የሚመረኮዝ በመሆኑ ከጊዜ ጊዜ ሊለያይ ይችላል፡፡

## ተግባር ሁለት፡ ለአድቮከሲ ሥራ የሚሆኑ ጉዳዮችን መምረጥ

የአድቮኬሲ ኮሚቴው አንዴ ከተቋቋመ በኋላ አድቮኬሲ የሚሠራባቸው ነጥቦች ሊኖሩት ይገባል፡፡ በመሆኑም የንግድና ዘርፍ ማኅበራት የሚቋቋሙት አባላቶቻቸውን ለማገልገል በመሆኑ አባላትን በምን ጉዳይ ላይ የአድቮከሲ ሥራ ሊሠራ እንደሚገባ መጠየቅ ተገቢ ተግባር ነው፡፡ ይህም የአባልነትን ፍላጎት ለይቶ የሚያወጣ ጥናትን በማካሄድ ሊሠራ ይችላል፡፡

የንግድ ማኅበራት ሊቀመናብርትና የአድቮከሲ ኮሚቴ አባላት እውቀትና ችሎታ ለአድቮከሲ ሥራ የሚሆኑ ነጥቦችን ለማግኘት የሚረዳን መጠይቅ በማዘጋጀት ዙሪያ የታነጸ ሊሆን ይገባዋል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በመደበኛነት ከፖሊሲ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚከታተሉና ከሕግ አውጪና ሕግ አስፈፃማዎች ጋር የሚገናኙ መሆን አለባቸው፡፡ በዚህም የተነሳ እነዚህ ወገኖች ወደፊት ሊደረጉ ስለታቀዱ ከፖሊሲ ጋር የተያያዙ ጠቃሚ ጉዳዮች ከአባላት በበለጠ ግንዛቤ ያላቸው ነው የሚሆኑት፡፡ (ይህ መረጃ በኢሜል፣ በኒውስሌተር፣ በበራሪ ወረቀቶችና በመሳሰሉት በመደበኛነት ለአባላት ሊደርስ ይገባል፡፡)

በዚህ መረጃ እና በሚከተሉት መስፈርት ላይ በመንተራስ አንገብጋቢና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች አባላት በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ የሚረዱ ዝርዝር መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ገበያ ቀመስ ማሻሻያዎችንና ነጻ የንግድ ድርጅቶችን ከማበራታት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣
- አንዱ ጉዳይ በርካታ ቁጥር ላላቸው የማኅበሩ አባላት አንገብጋቢ ሆኖ ሲገኝ፣
- ከአንድ ከተወሰነ ፖሊሲ፣ ሕግ ወይንም ደንብ ጋር የተያያዙ ችግሮች ሲኖሩ (መተንበይ በማይቻል ሁኔታ በበርካታ ቦታዎች የሚከሰቱ ጉዳዮችን ሳይጨምር)
- አስቸጋሪ ስለመሆናቸው የማያሻሙ ጉዳዮች፣
- በአጭር ጊዜ ውስጥ የመሳካት እድል ያላቸው ጉዳዮች (በሌላ አገላለጽ የተወሰኑ የፖሊሲ መነሻ ሐሳቦችን በማቅረብ ሊፈቱ እና ሊስተካከሉ የሚችሉ ጉዳዮችን ማለት ሲሆን፣ ሕገ መንግሥትን ወይንም አጠቃላይ የሕግ አወጪውን ሥርዓት መፈተሽን የሚጠይቁ ነጥቦችን አያካትትም፡፡)
- በአብላጫው የማኅበሩ አባላት እና ቦርድ አባላት ተደጋፊነት ያገኙ ጉዳዮች ሲሆኑ፣(እርስ በእርሳቸው የሚጣረዙ ጉዳዮችን ማስወገድ አስፈላጊ ነው፡፡)

- የኃይል ሚዛን ባላቸው ቡድኖች ወይንም ሕግ አውጪዎች ወይንም በብዙሃኑ ተቃውሞ የማይገጥማቸው ጉዳዮች ሆነው ሲገኙ፣
- የማህበሩን ክብርና ዝና የማያጐድፉ ጉዳዮች መሆናቸው የተረጋገጠ ነጥቦች ሆነው ሲገኙ::

## የጥናት መጠይቆችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት

በአጭሩ ከላይ በተጠቀሱት መስፈርቶች ላይ እና ከንግድ ማኀበራት መሪዎች እና ከአድቮከሲ ኮሚቴ አባላት በሚገኙ ግብአቶች ላይ ተንተርሶ የጥናት መጠይቆችን በማዘጋጀት ለሁሉም የማኀበሩ አባላት ሞልተው እንዲመልሱ መላክ አስፈላጊ ነው:: መጠይቁ አባላት የሚከተሉትን እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ሊሆን ይገባል:-

- የተወሰኑ ሊነሱ የሚገባቸውን ነጥቦች በአንገብጋቢነታቸው ቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ፣
- ለእያንዳንዱ ነጥብ የተጠቆሙ የመፍትሔ ሀሳቦችን በደረጃ እንዲያስቀምጡ፣
- መጠይቁን በተጠየቀው የጊዜ ገደብ ሞልተው እንዲመልሱ::

የሚቻል ከሆነ የዚህ ዓይነት መጠይቆች የአድቮከሲ ኮሚቴው በትክክል የአባላቱን ጉዳዮች እያነሳ መሆኑን ለማረጋገጥ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ሊዘጋጁ ይገባል:: (የአሜሪካ ንግድ ምክር ቤት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ**2003-2004** ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ጉዳዮችን ለማጥናት ያሠራጨውንና አባሪ «ሀ»በሚል የቀረበውን ይመልከቱ::)

## የአትኩሮት ቡድን ስብሰባዎችን ማካሄድ

ቁልፍ ጉዳዮችን ለመምረጥ ሌላው መንገድ የአድቮኬሲ ኮሚቴ አባላት ከጥቂት የማህበራት አባላት ጋር ተገናኝተው አባላቱን በሚመለከቱ ፖሊሲዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ ነው:: እያንዳንዱ የሚቋቋመው ቡድን በአንድ የአድቮኬሲ ኮሚቴ አባል የሚመራ ሆኖ ይህም ግለሰብ ውይይቱ የንግድ እንቅስቃሴን ወደሚመለከቱ ጉዳዮች እንዲያማትርና /ቀደም ብሎ በተጠቀሱት መስፈርት መሰረት/ ብሎም ለእያንዳንዱ ጉዳይ ቀጥተኛ መፍትሔ የሚያመላክት እንዲሆን ማስቻል ይኖርበታል::

## የአድቮከሲ *ሥራን* ቀድመው የሚሹ ጉዳዮችን መምረጥ /መለየት

እንደሚታወቀው የአድቮከሲ ኮሚቴው የእያንዳንዱን አባል ጉዳይ በተናጠል በመያዝ የአድቮኬሲ *ሥራ* አይሠራም:: በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት የአድቮከሲ ኮሚቴው ባልደረቦች ጉዳዮቹን ጠበብ አድርገው ለማሰባሰብ እንዲችሉ ከዚህ የሚከተሉትን ማከናወን አለባቸው::

- የጥናቱን ውጤትና ከሚመለከታቸው ባለጉዳዮች ጋር የተደረገውን ውይይት ሃሳብ በአንድ ገጽ ላይ በዝርዝር ማዘጋጀት፣

- በእያንዳንዱ የአድቮከሲ ሥራ ሊሠራበት ቅድሚያ በተሰጠው ጉዳይ አንጻር በጀቱ በቂ ኃይልን ለማንቀሳቀስ ይበቃ እንደሆነ ማረጋገጥ፣
- በአንገብጋቢነታቸው ቅደም ተከተል በስተመጨረሻ የተቀመጡትን የአድቮከሲ ነጥቦች ለእያንዳንዳቸው በቂ በጀት እስኪገኝ ድረስ ከዝርዝሩ ማውጣት፣
- አንገብጋቢ ናቸው ተብለው ቅድሚያ የተሰጣቸውን ጉዳዮች በዝርዝር በማስቀመጥ ከጐኑም ፖሊሲውን ለማሻሻል የተሰጡትን የመፍትሄ ሃሳቦች መዘርዘር (ፖሊሲውን ለማሻሻል የመፍትሄ ሃሳብ ናቸው ተብለው የቀረቡት ነጥቦች አጭርና ቀላል መሆን አለባቸው:: በፖሊሲው ላይ የተሰነዘሩ የመፍትሄ ሃሳቦችን ይበልጥ ለማጠናከርና ተጨባጭ ማስረጃዎችን ለማቅረብ ተከታታይ ጥናቶች መሠራት አለባቸው):: እዚህ ላይ አንዳንድ ነጥቦች የግድ አዲስ ፖሊሲ ወይንም አዋጅ እንደማይፈልጉና ያለውን ሕግና ፖሊሲ የአፈጻጸም ሥርዓት ማስተካከል ብቻ ሊፈልጉ እንደሚችሉ ማወቅ ያስፈልጋል::
- ይህንንም ዝርዝር ለማጸደቅ ለማኅበራት ቦርድ መላክ::

ማኅበራት አንድ ጊዜ በአባለቶቻቸው የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ በሚያሳድሩ እና በተመረጡ ፖሊሲዎች ላይ ጫና የሚፈጥር የአድቮከሲ ሥራ ለመሥራት ከተንቀሳቀሱ ሥራውን በተዋጣ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ መጀመር አለባቸው:: ይህም የአድቮከሲ ሥራን መሥራት አዋጪ እንደሆነ ለማኅበሩ አባላት ለማሳየት ይረዳል:: የአድቮከሲ ኮሚቴው አንድ ጊዜ አድቮከሲ በሚሠራባቸው ጉዳዮች ላይ ቴክኒክና ስልቶቹን ከቀየሰ አስቸጋሪ ወደሆኑና ጊዜ ወደሚፈልጉቱ ጉዳዮች ፈጥኖ መግባት ይኖርበታል::

---

## *የሕዝብ አመለካከት ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው::*

*የህዝብ አስተያየትና አመለካከት ፖሊሲ አውጪዎች በሚሰጡት ወሳኔ ላይ ከፍተኛ ተጽንኦ መፍጠር ይችላል:: የአድቮከሲ ኮሚቴው ባልደረቦች ማኀበሩ ጥያቄ እያነሳባቸው ባሉ ጉዳዮች ላይ የሕዝቡ አስተያየት ምን እንደሚመስል ማወቅ አለባቸው:: ይህን ጠንቅቆ ማወቅ የአድቮከሲ ኮሚቴው ሕዝቡ በማይቀበለውና ለሕዝቡ በማይስማማው ጉዳይ ላይ የአድቮከሲ ሥራን ሠርቶ አላስፈላጊ ለሆነ ወጪ እንዳይዳረግ የሚጠብቀው ሲሆን፣ የማይወጡትን እና በአሸናፊነት የማይጨርሱትን ጦርነት እንደአለመጀመርም ይቆጠራል:: የሕዝብን አመለካከት ለመለካት በርካታ መንገዶች አሉ:: በመጀመሪያ የአድቮከሲ ሥራ ሊሠራበት በታቀደው ጉዳይ ላይ ጥናቶች መሠራታቸውንና የሕዝብ አስተያየቶች መሰብሰባቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህ ከሆነ የኮሚቴው አጋዥ ሠራተኞች ጥናቱ የተደረገበት ሥልት ትክክል መሆኑንና ውጤቱም ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው:: ጥናቶች ካልተሰሩ የኮሚቴው ሠራተኞች ወይንም አስፈላጊ ከሆነ ባለሙያዎች ተቀጥረው የሕዝቡ አስተያየት ምን እንደሚመስል መጠይቅ በማዘጋጀት ወይንም ከሚመለከታቸው ጋር ውይይት በማካሄድ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል::*

---

## ተግባር አምስት፡ የአድቮኬሲ እቅድን ማውጣትና መተግበር

በዚህ ወቅት የአድቮከሲ ኮሚቴ አባላት ቅድሚያ የሚሰጣቸውንና አንገብጋቢ ናቸው የተባሉትን ነጥቦች ለይተው ይጨርሳሉ:: የሚቀጥለው ተግባር እቅድ መንደፍ ነው:: እቅዱ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ፖሊሲዎችን አስመልክቶ የተዘጋጀው ግብ ላይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመድረስ እና ይኼንኑም ለመተግበር የሚያስችሉ መሣሪያዎችን የያዘ መሆን አለበት:: በመጀመሪያ ማለትም በዚህ ክፍል የተለያዩ ጠቃሚ የሆኑ የአድቮከሲ መሣሪያዎች ይዘረዘራሉ:: ቀጥሎ ማለትም ከዚያ በኋላ ባለው ተግባር ስድስት ደግሞ የአድቮከሲ ኮሚቴው ሠራተኞች ማኅበሩ የአድቮከሲ ሥራውን ለመሥራት ያቀደውን እቅድ ከግቡ ለማድረስ ወሳኝ የሆኑ መሣሪያዎችን ካዘጋጁ በኋላ በምን ያህል የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ ሊተገብሩት ይገባል የሚለውን እናያለን::

### አጋዥና ቁልፍ የሆኑ ጉዳዮችን መለየት

ማህበሩ የሚሠራው የአድቮከሲ ሥራ ውጤታማ እንዲሆን የማኅበሩ አባለት የፖሊሲ አወጣጡ ሂደት እንዴት እንደሚሠራና ለእያንዳንዱ ለሚገባው ጉዳይም ቁልፍ የሆነው ነጥብ ምን እንደሆነ ማወቃቸው እጅግ በጣም አስፈላጊያቸው ነው፡፡ በእየንዳንዱ አንገብጋቢ ነው የሚል ቅድሚያ በተሰጠው ነጥብ ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘረውን መመሪያ በመከተል የአድቮከሲ ኮሚቴ አባላት ፖሊሲ እንዴት እንደሚቀረጽ የተሟላ እውቀት ሊያገኙ የሚችሉ ሲሆን፣ ውጤታማ የሆነ የአድቮከሲ ሥራን ለመሥራትም ያስችላቸዋል::

አንደኛ. ከሚከተሉት ውስጥ ጉዳዩ በየትኛው ደረጃ እንደሚገኝ መወሰን

- ክፍለ ከተማ
- ክልል
- በብሄራዊ ደረጃ

ሁለተኛ. ጉዳዩ ከዚህ ከሚከተሉት ውስጥ ከየትኛው ጋር ግንኙነት እንዳለው ለይቶ ማወቅ

- ከሕግ አውጪ፣
- ከፍትህ አካላት፣
- ወይንስ ከሕግ አስፈጻሚ::

የኮሚቴው ሠራተኞች ጥያቄ የተነሣበት ጉዳይ አንድ ጊዜ በየትኛው ደረጃና የትኛውን አካል እንደሚመለከተው ካለዩና ካወጡ በኋላ ማኅበሩ በሚገኝበት ሀገር የፖሊሲ አወጣጡ ሂደት እና የሚነሳው ጥያቄ ግንኙነት ምን እንደሚመስል አብጠርጥረው ማወቅ አለባቸው:: የኮሚቴው ሠራተኞች በተመረጠው ነጥብ ላይ የፖሊሲ አወጣጡን ሂደት በሚተነትኑበት ጊዜ ከማኅበሩ

አቅም አንጻር ተጽእኖ ማሳረፍ የሚፈልጉባቸውን ወሳኝ ነጥቦች ከመለየትና ቁልፍ ፖሊሲ አውጪዎች እነማን እንደሆኑ ከመረዳት አንጻር ተጠቃሚ ይሆናሉ:: እነዚህን ዝርዝር ጉዳዮች የያዘው መረጃም በተገቢ ሁኔታ መጠበቅና አስፈላጊ በሚሆንበትም ጊዜ ወቅታዊነቱን እንዲጠብቅ መሻሻያ ማድረግ አለበት::

### የእያንዳንዱን ጉዳይ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎችን መለየት

የተዋጣለት አድቮከሲ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ማን ደጋፊ፣ ማን ተቃዋሚ እንደሆነ እና ለምንስ እንደሚቃወም ለይቶ ማወቅን ይጠይቃል:: ቀድሞ ተለይተው በወጡት ወሳኝ በሆኑት ጉዳዮች ላይ በመንተራስ የኮሚቴው ሠራተኞች በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ቁልፍ የሆኑት ፖሊሲ አውጪዎች ያላቸውን አቋም ማወቅ አለባቸው:: ይህንንም የፖሊሲ አውጪዎቹ ቢሮ የሚያሳትማቸውን ሕትመቶችና መግለጫዎች እንዲሁም ድረ ገጻቸውን በመከታተልና እነርሱ ቢሮ ከሚሠሩ ሠራተኞች ጋር ስለ ጉዳዩ በመነጋገር እና መረጃ በማሰባሰብ ለማወቅ ይቻላል:: በዚህ መልኩ የሚገኘውን መረጃ በሚገባ በማደራጀት እያንዳንዱ የፖሊሲ ውሳኔ ሰጪ አካል ምን እንደሚያስብ በቀላሉ ለማወቅ ይቻላል:: አስፈላጊ ከሆነም በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ የትኛው ፖሊሲ አውጪ ደጋፊ፣ የትኛው ተቃዋሚ እንደሆነና የትኛው ውሳኔ እንዳሰጠ የሚያሳይ ሰንጠረዥም ማዘጋጀት ያስፈልጋል::

የፖሊሲ አውጪዎች አቋም አብዛኛውን ጊዜ ዋና ዋና ተጠቃሚ ቡድኖች በአንድ ጉዳይ ላይ በያዙት አቋም ተጽንኦ ስለሚደረግበት የአድቮኬሲ ኮሚቴ አባላትም እንደዚህ አይነቶቹን ተጠቃሚ ቡድኖች የጉዳዩ ደጋፊዎች ወይንም ተቃዋሚዎች መሆናቸውን ለይተው ማወቅ ይኖርባቸዋል::

ይኼንኑ ጉዳይ አስመልክቶ እነዚህ ተጠቃሚ ቡድኖች የተነሳውን ጥያቄ በመደገፍም ሆነ በመቃወም ያላቸውን አቋም ሊያውቁ ይገባል:: የኮሚቴው ሠራተኞች እያንዳንዳቸው ቁልፍ የሆኑ ቡድኖች ያላቸውን አቋም እና ለምን የዚያን ዓይነት አቋም እንደያዙ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል:: ይህንንም አይነት መረጃዎች ከእያንዳንዱ ወሳኝ ከሆነው ቡድን ሕትመቶችና ሌሎች ሰነዶች ማግኘት የሚቻል ሲሆን፣ አስፈላጊ ከሆነም የእነዚህን ቁልፍ የሆኑ ቡድኖችን ከፍተኛ ተወካዮች በጉዳዩ ላይ ቀርቦ ማነጋገር ይቻላል:: በዚህ ጥረት ላይ በመንተራስም የኮሚቴው ሠራተኞች ጉዳዩን አስመልክቶ የሚደግፉ ፣ የሚቃወሙና ውሳኔ ያልሰጡ ወገኖችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ማዘጋጀት አለባቸው::

በመሆኑም የአድቮኬሲ ኮሚቴ ሠራተኞች፣

- ጉዳዩን አስመልክቶ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው ውሳኔ ሰጪዎች እነማን እንደሆኑ ያውቃሉ፣
- ጉዳዩን አስመልክቶ ተጽእኖ በማሳረፍ ዙሪያ ድርሻ ያላቸው ቁልፍ ተሳታፊዎች እነማን እንደሆኑ ይገነዘባሉ፣

- የፖሊሲው አቅጣጫ ወደየት እየሄደ እንደሚገኝ ይረዳሉ፡፡

የኮሚቴው ሠራተኞች ይኼንን መረጃ ጠንካራና ውጤታማ የሆነ የአድቮከሲ እቅድ ለመንደፍ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

## መልዕክትን ለታዳሚዎች በሚስማማ መልኩ መቅረጽ

ውጤታማ የሆነ የአድቮከሲ ስልት ወይንም እቅድ ከተለያዩ ታዳሚያን ጋር የተሳካ ግንኙነት መፍጠርን ይጠይቃል፡፡ ይህም ፡-

- በፖሊሲው ነጥብ ዙሪያ ገና ውሳኔ ያልሰጡትን ወገኖች ድጋፍ ለማግኘት፣
- ጉዳዩን ከመጀመሪያ ጀምሮ እየተቃወሙት ያሉትን ግለሰቦችና ቡድኖችን ድጋፍ ለማሰባሰብ፣
- ከመሠረቱ ጉዳዩን የሚደግፉ ወገኖችን ለማጠናከር፣

ይኼንን ለማሳካት እና የአድቮከሲውን ሥራ ለመሥራት የሚዘጋጀው ሰነድ ተጽእኖ እንዲያርፍባቸው የሚፈለጉ ወገኖችን ኢላማ ያደረገና ወቅቱንም ጠብቆ የሚደርስ ሊሆን ይገባል፡፡ የእነዚህን ወገኖች አመለካከት ለመቀየር እና ሃሳቡን እንዲቀበሉ ለማድረግ ለምሳሌ በአንድ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ አጭርና ግልጽ የሆነ ማብራሪያ ማዘጋጀት የሚቻል ሲሆን በሌላ ጊዜ ደግሞ ጥልቀት ያለው አገላለጽ ያለው ጽሑፍ ለማቅረብ ይቻላል፡፡

የሚዘጋጀው መልዕክት ግን በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ የግድ፡-

- ለአድማጩ የግል ፍላጐት የቀረበ መሆን አለበት፣
- ጉዳዩ ለምን ጠቃሚ እንደሆነና ለምን የተያዘው አቋም እንዲደገፍ እንደተፈለገ የሚያሳምን መሆን አለበት፣
- ግልጽ መሆን አለበት፣
- አስፈላጊ ከሆነም ቀጥሎ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ማመላከት አለበት፣
- የሚነሱ ጥያቄዎችን መልሶች ማካተት አለበት፡፡

ለፖሊሲ አውጪዎች የሚተላለፈው መልዕክት ደግሞ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

- ይህ ጉዳይ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ፣
- ምን ያህል ሕዝብ ወይንም ቡድን እንደሚደግፈው /እዚህ ላይ የተሰባሰበ የጉዳዩ ደጋፊዎች ፊርማ ቢኖር ይበልጥ አሳማኝ ይሆናል/
- የፖሊሲው መነሻ ሃሳብ ጠቃሚና ጐጂ ጐኖች ምን፣ ምን እንደሆኑ፣
- የፖሊሲው ረቂቅ ሠራተኞችን፣ ባለሀብቶችን አቅራቢዎችንና ሸማቾችን የመሳሰሉ ወገኖችን ምን ያህል እንደሚጐዳና እንደሚጠቅም፣
- ሊወሰድ የታሰበው እርምጃ ከፖሊሲ አውጪዎች የፖለቲካ መሠረት አንጻር ሲታይ ምን አንደምታ እንዳለው፣

- ምን ዓይነት የተወሰኑ እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚገባ፣(ለምሳሌ የትኛው ፖሊሲ፣ አዋጅ ወይንም መመሪያ ሊጠበቅ፣ ሊሰረዝና ሊሻሻል እንደሚገባ)
- የቀረበውን ፖሊሲ፣ አዋጅ እና መመሪያ አስመልክቶ የተወሰነ ቋንቋ ወይንም ትክክለኛ ረቂቅ::

የሚተላለፈው መልዕክት ለሚፈለገው ወገን በትክክል እንዲደርስ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ መንገዶች አሉ:: እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ::

- ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣
- መግለጫዎች፣
- የፖሊሲ አቋም ማሳያ ጽሑፎች፣
- የጋዜጣው ርዕሰ አንቀጽ በሚቀርብበት ገጽ በተቃራኒው የሚታተሙ ጽሑፎች፣
- በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችን የሚመልሱ የእውነታ ማሳያ ጽሑፎች፣
- ንግግሮች /ለጉባኤ ፣ ለወርክሾፕ ፣ ሴሚናሮችና ኮንፍረንሶች የተዘጋጁ/
- ለመገናኛ ብዙሃን የሚዘጋጁ የሚዲያ ሰነድ መያዣዎች

ከላይ የተዘረዘሩትን መርጃ ጽሁፎች በማዘጋጀት በተቻለ ፍጥነት ለሚመለከታቸው ወገኖችና ቁልፍ ለሆኑ ፖሊሲ አውጪዎች መላክ ማኅበሩን ፖሊሲው ላይ ጥሩ የክርክር መድረክ እንዲፈጥር የሚያደርገው ሲሆን፣ ውጤት የማምጣት ተስፋውንም የሰፋ ያደርገዋል:: የአድቮከሲ ሥራ ዋናው ዓላማም ይኸው ነው::

---

### *የአድቮከሲ እቅድ ሲዘጋጅ ሊነሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች*

- *ለውጥ የሚያስፈልገው ነገር ምንድ ነው?*
- *ለውጡን እንዴት ማካሄድ ይቻላል?*
- *ምን ያህል ለውጦች መካሄድ አለባቸው?*
- *ለውጡ መቼ መካሄድ አለበት?*
- *ለውጥ የሚያስፈልገውን ጉዳይ እንዴት ማዘጋጀት ይቻላል?*
- *ለውጡ እንዴት ሊተገበር ይችላል?*

---

## ተለይተው አትኩሮት የተደረገባቸውን የአድቮኬሲ መሳሪያዎች ስለማዘጋጀት

### *መርጃ ቁጥር 1: ጋዜጣዊ መግለጫ*

ለመገናኛ ብዙሃን የሚላክ ጋዜጣዊ መግለጫ ወይንም ፕሬስ ሪሊዝ የአድቮከሲ ሥራ ቁልፍ መሳሪያ ነው:: ለመገናኛ ብዙሃን ይህን ሰነድ መላክ በጣም ጠቃሚ ነው:: መግለጫውን ለማኅበሩ አባላት እና በማኅበራት ውስጥ የመንግሥት ተወካይ ለሆኑት መላክ የአድቮከሲ ሥራ

እየተሠራበት ላለው ነጥብ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ የሚከተለው መመሪያ ፕሬስ ሪሊዝ እንዴት እንደሚዘጋጅ የሚያስረዳ ነው፡፡

## የተዋጣለት ጋዚጣዊ መግለጫ አዘጋጃጀት መመሪያዎች

ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎችን በተቃና መልኩ ለማሳካት ማኅበሩ በሚያነሣው ቁልፍ በሆነ ጉዳይ ላይ ለአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ትምህርት መስጠት መልካም ነው፡፡ ይህን ማድረግም ከሕዝቡ የሚሰነዘሩ በተቃራኒው ያሉ ሃሳቦችን ለማስቀየርና በራስ ወገን ለማሰለፍ ይረዳል፡፡ የዚህ ዓይነቱን ተግባር ለማሳካት ቀላሉና ዝቅተኛ ወጪ ያለው አካሄድ በሥራ ላይ ያሉ ሕትመቶችን እና ሬዲዮና ቴሌቭዥኖችን መጠቀም ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን አጋዥ ኃይሎች በተዋጣለት መልኩ ለመጠቀም የማኅበሩን ጉዳዮች የዜና ሽፋን በሚሰጧቸው ጋዜጠኞችና በማኅበሩ መካከል አስተማማኝ የሆነ ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ጋዜጠኞች ዘንድ ለመድረስ ዋናው መንገድ ታዲያ ፕሬስ ሪሊዝ ነው፡፡

### ለመገናኛ ብዘሃን የሚላክ ጋዜጣዊ መግለጫ (Press Release )

ፕሬስ ሪሊዝ እንዲተላለፍ የተፈለገን መልእክት በትክክል ጋዜጠኞች ዘንድ እንዲደርስ የሚያስችል የተለመደ መንገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይኼንኑ ውጤታማ ለማድረግ መመሪያዎችን መከተል ያስፈልጋል፡፡ መመሪያውን መከተል የሚላከውን ጋዜጣዊ መግለጫ ከሌሎች ከሚላኩ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ተመራጭ የሚያደርገው ሲሆን፣ ሕዝብ ዘንድ ተመራጭ ዜና በማድረስ ላይ የሚያተኩሩትንም ጋዜጠኞች ቀልብ ለመሳብ ይረዳል፡፡

### የጋዜጣዊ መግለጫ ቁልፍና መሠረታዊ ነጥቦች

**1ኛ. ግልጽነት፡-** የሚላከው ጋዜጣዊ መግለጫ ጋዜጠኞች መሠረታዊ ነጥቦችን ወዲያውኑ እንዲረዷቸው ሆኖ ሊዘጋጅ ይገባዋል፡፡ የድርጅቱ ወይንም የማኅበሩ ስምና ዓርማ በመግለጫው አናት ላይ መስፈር አለበት፡፡ መግለጫው የተሠራጨበት ቀን እንዲሁም ጋዜጠኞች ግልጽ ያልሆነላቸው ጉዳይ ሲኖር የሚያነጋግሩት ሰው ስምና ስልክም አብሮ በገጹ አናት ላይ መስፈር ይኖርበታል፡፡ መግለጫው ጉላ ተብሎ የተጻፈና ሃሳቡን ጠቅልሎ የያዘ ርዕስ ሊኖረው ይገባል፡፡ ርዕሱ ጋዜጦች ላይ ከሚወጡት ርዕሶች ጋር የሚመሳሰል መሆን አለበት፡፡ የጋዜጣን ዜና ርዕሱን በመመልከት ብቻ ስለምን ጉዳይ እንደሚያወራ ፈጥኖ ለመረዳት እንደሚቻለው ሁሉ የጋዜጣዊ መግለጫም ርእስ በቀላሉ ሊረዱት የሚችልና ኃሳቡን ጨምቆ የያዘ መሆን አለበት፡፡ ይህ ካልተደረገና መልዕክቱ በግልጽ የተቀመጠ ካልሆነ ጋዜጠኞቹ ለማንበብም ፍላጎት አያድርባቸውም፣ ለመረዳትም ይቸገራሉ፡፡

**2ኛ. ምጥንነት፡-** ጋዜጣዊ መግለጫ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ከአንድ ገጽ መብለጥ የለበትም፡፡ ሲጻፍ ግን እንዲነበብና ለጋዜጠኞችም አሰራር እንዲመች ዘርዘር ተብሎ መፃፍ አለበት፡፡ መግለጫው ከአንድ ገጽ እንዳይዘል ሆኖ ዘርዘር ብሎ መፃፍ ያለበት ሲሆን፣ አንአንዳንድ ጊዜ ግን ጠቅጠቅ ማድረግም ይቻላል፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫዎች ላይ ብዙውን ጊዜ በርካታ ነጥቦችን የማካተት ዝንባሌ ይኖራል፡፡ ነገር ግን አንገብጋቢ የሆኑና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ነጥቦች ላይ ብቻ ማተኮር አስፈላጊ ነው ፡፡ ምክንያቱም የመግለጫው ዋና ዓለማ ወሳኝና አስፈላጊ የሆኑትን ጭብጦች ብቻ ለጋዜጠኞች በመላክ እነርሱ ፍላጐት አድሮባቸው ዝርዝር ጉዳዮችን እንዲጠይቋችሁ ማድረግ ነውና፡፡

**3ኛ. ትንታኔዎች/ ዝርዝሮች፡-** የትኛው ቁልፍ የሆነ ኢንፎርሜሽን ተካቶ የትኛው ይቅር ብሎ መወሰን ሁሌም አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ ለዚህ ግን ልንከተለው የሚገባን እና ልናነሳቸው የሚገቡን ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነዚህም ጥያቄዎች ምን ለማለት ነው የፈለኩት? እኔ ማን ነኝ? ይሄ መች ነው የሚካሄደው? መቼ ነው የሆነው? ለምንድን ነው አስፈላጊ የሆነው? የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁሉንም የግድ መከተል ላያስፈልገን ይችላል፡፡ ነገር ግን ምንም ነገር ላለመርሳት ሲባል በደንብ ብንመለከታቸው መልካም ነው፡፡ በተጨማሪም በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነጥብ በማንሳት እነዚህን ጥያቄዎች መዳሰስ ያስፈልጋል፡፡

**4ኛ. ቅርጽ/ይዘት/** ፡-_ከላይ ከተጠቀሱት የአጻጻፍ ሕጐች በተጨማሪ ጋዜጣዊ መግለጫ ደረጃውን የጠበቀ ቅርጽ ወይንም ይዘት ሊኖረው ይገባል፡፡ መቼም ቢሆን የሚቻል ከሆነ በመጀመሪያው ወይንም በሁለተኛው አንቀጽ ላይ በጉዳዩ ላይ ተሳትፎ ያለውን የኮሙዩኒቲ መሪ ወይንም የማኀበሩን አባል ንግግር በአጭሩ በጥቅስ መልክ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ የመጨረሻው አንቀጽ ደግሞ በአጭሩ ስለማኀበሩ ወይንም ስለድርጅቱ መረጃ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡ የጋዜጣዊ መግለጫው ገጽ መጨረሻ ጋዜጠኞች ከዚያ ገጽ ውጪ ሌላ ገጽ እንደሌለ እንዲረዱና ጽሑፉ ማለቁን እንዲያውቁ የሚያደርግ ምልክት ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ በአሜሪካ -30- ወይንም ### የሚሉ ምልክቶች እንደገጽ መዝጊያ ያገለግላሉ፡፡

**5ኛ. ድርጊት፡-**_ጋዜጣዊ መግለጫ የአንድን ድርጊት መከናወን ለማብሰር የሚላክ ከሆነ በግብዣ መልክ መዘጋጀትና መላክ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ፣ ለጋዜጠኞች በግብዣ መልክ ከሚላከው ጋዜጣዊ መግለጫ በተለይ ለአባላት የሚላከው እንደማንኛውም ጋዜጣዊ መግለጫ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህም ለአባላት የሚላከው መግለጫ የድርጅቱ ዓርማና ስም በገጹ አናት ላይ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በማስከተልም አስፈላጊ ከሆነ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን በስም በመጥቀስ በእንዲህ ያለ ጉዳይ ላይ ፣ በእንዲህ ያለ ቦታ፣ በእንዲህ ያለ ቀንና ሠዐት

እንዲገኙ በሚል አክብሮት በሚገልጽ መልኩ ጉላ ተደርጐ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡ ነጥቡን በአንድ ዓረፍተ ነገር አጠጋግቶ መጻፍ የእለቱ እንግዳ ተናጋሪ ማን እንደሆነና ጉዳዩ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ በቀላሉ ለማመልከት ይረዳል፡፡ በመጨረሻም በስብሰባው ላይ የሚገኙ ከሆነ ያሳውቁን የሚል መልእክትና መልዕክቱን የሚያስተላልፍ ሰው ስምና አድራሻ መቀመጥ ይኖርበታል፡

## *ጋዜጣዊ መግለጫን ስለማሰራጨት*

ጋዜጣዊ መግለጫው በሚላክበት ጊዜ ለተወሰኑ ጋዜጠኞች በስማቸው መድረስ አለበት፡፡ አንድ እለትን አስመልክቶ የተዘጋጀውን ይሄንኑ ጋዜጣዊ መግለጫ በማስታወስ በማለት በሳምንት ጊዜ ውስጥ ደግሞ መላክ ጥሩ ነው፡፡ ጋዜጠዊ መግለጫው አንዴ ከተላከ በኋላ ጋዜጠኞቹን በመደወል መጐትጐት መፍራት የለበትም፡፡ መግለጫው ለሁሉም የህትመት፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ተቋማት መላክ አለበት፡፡ በጊዜ ሂደት ውስጥ መግለጫዎቹ ከሚያትሙ ጋዜጠኞች ጋር ጥሩ ግንኙነት ይፈጠራል፡፡ ጋዜጠኞቹም ልክ አንደ አንድ የዜና ምንጭ ስለሚቆጥሯችሁ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ፡፡

<u>የሚከፈለው መገናኛ ብዙሃን፡-</u> በተቻለ መጠን ያለምንም ክፍያ ጉዳዩን እንደዜና ቆጥረው መረጃችሁን በሚያሠራጩላችሁ መገናኛ ብዙሃን መጠቀም የተሻለ ነው፡፡ የሰዎች አመለካከትና አስተሳሰብ ላይ ተጽእኖ ከማሳደር አንጻር ያለ ክፍያ መረጃዎችን የሚያሠራጩ መገናኛ ብዙሃን ተማራጭ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ክፍያ በመቀበል ራሳችሁ ያዘጋጃችሁትን ዜና የሚያሰራጩላችሁን ወይንም በማስታወቂያ መልክ የሚያስተላልፉላችሁን መገናኛ ብዙሃን መጠቀም ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ እንደየሀገሩ ሁኔታም ምናልባት አንዳንድ የዜና ዘጋቢዎች ዜናውን ለመሥራት ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ ደረሰኝ ተቀባይ «checkbook journalism» እየተባለ የሚጠራው በክፍያ መረጃን የማሠራጨት ተግባር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ሙሉ በሙሉ መወገድ ይኖርበታል፡፡

## *መርጃ ቁጥር 2* ፡ አጭር መግለጫ /ማህፀረ -ጉዳይ

ሌላው የአድቮኬሲ ሥራ ለማከናወን ጠቃሚው መሣሪያ «Issue brief» የሚባለውና የጉዳዩን ጭብጥ በአጭሩ የሚዘረዝር ጽሑፍ ነው፡፡ ይህ ጽሑፍ በአጭርና ከአንድ እስከ ሁለት በሚደርስ ገጽ የሚዘጋጅ ማጠቃለያ ሲሆን፣ ነጥቡ ለምን አስፈላጊ እንደሆነና በአጭር ጊዜ ውስጥ ይኼንኑ አስመልክቶ ምን መደረግ እንዳለበት የሚጠቁም ነው፡፡ ይህ አይነት መግለጫ ውጤታማ እንዲሆን ከዚህ በሚከተለው ዓይነት መዘጋጀት አለበት፡፡

- ጉዳዩን ወይንም ችግሩን ለይቶ በማውጣት እና በማጉላት ከሕግና ደንብ አንጻር የዚያ ጹሑፍ አንባቢ አጭርና ግልጽ በሆነ መልኩ እንዲረዳ ማድረግ፡፡ የሚገኝ ከሆነም የጉዳዩን ወይንም የነጥቡን የሕግ ሂደት ማካተት ተመራጭነት አለው፡፡

- ለጽሑፉ ታዳሚዎች ጉዳዩ ለምን በጣም አንገብጋቢ እንደሆነና የንግድ እንቅስቃሴንም እንዴት ሊያውክ እንደሚችል ግልጽ በሆነ አቀራረብ ማስቀመጥ ያሻል፡፡ ለምሳሌ አንባቢው የማያውቃቸውንና በቀላሉ የማይረሳቸውን የኢኮኖሚ ቃላት መጠቀም ይቻላል፡፡ በተቻለ መጠን የወጣው ሕግና ደንብ እንዴት ጽሑፉ የተዘጋጀለትን ወገን ብሎም አጠቃላይ ሕዝቡን እንደጐዳ የሚያሳዩ ግራፎችና ቻርቶችን መጠቀም ጉዳዩን በተገቢ ሁኔታ በዓይናቸው እንዲያዩት ስለሚያስቻል አስፈላጊ ነው፡፡
- ያለውን ወይንም የተፈጠረውን ችግር በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማቃለል የሚረዱ የፖሊሲ የመፍትሔ ሃሳቦችን ማካተት ያስፈልጋል፡፡ የተጠቆመው የፖሊሲ የመፍትሔ ሃሰብ እንዴት ሊጠቅም እንደሚችል የሚያሳይ ቻርትና ግራፍ በማስደገፊያነት ማቅረብ ጠቃሚ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ የሚሰነዘረው የመፍትሔ ሃሳብ ችግሩን ለማቃለል ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

**መርጃ ቁጥር 3፡- የፖሊሲ አቋም የማሳወቂያ ጽሁፍ**

ሌላው የአድቮከስ *ሥራ መርጃ መሣሪያ* በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ ያላቸው ሆነው ረዘም ያለ ጽሑፍ የማንበብ ልምድ ያላቸውን ሰዎች ለማሳመን የሚዘጋጀው የፖሊሲ አቋምን የሚገልፀው የፖሊሲ አቋም መግለጫ የተሰኘው ጽሑፍ ነው፡፡

ይህ የተወሰኑ ፖሊሲ አውጪዎችን ወይንም ችግሩ የነካቸውን ወይንም በጉዳዩ ተሳታፊ የሆኑ የማኅበራት አባላትን ጭምር የሚያካትት ነው፡፡

በዚህ አቋም ማሳያ ጽሑፍ ላይ ጉዳዩን ብቻ በአጭሩ በሚያብራራው መርጃ ቁጥር ሁለት ላይ የቀረቡ ጭብጦችም እንዳሉ ይቀርባሉ፡፡ ይኸኛው ከዚያ የሚለየው ግን በአንድ ነጥብ ላይ ዘርዘር ያለ ማብራሪያዎችን፣ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እና ተጨማሪ ምሳሌዎችን ስለሚያካትት ነው፡፡ የፖሊሲ አላማን የሚያሳየው ይህ ጽሑፍ በዋናው ነጥብ ላይ የሚያተኩር ሆኖ ስሜትን የሚነካና ማሳመን የሚችል ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ይህ ጽሑፍ በአማካይ ከአምስት እስከ ስድስት ገጽ ይደርሳል፡፡

የአድቮከሲ መርጃ ጽሁፎች የሚከተሉትንም ያካትታሉ

መርጃ ቁርጥ 4 - የጋዜጣው አቋም ከሚቀርብበት ርእስ አንቀጽ በተቃራኒው በሚገኘው ተነባቢ ገጽ ላይ ጽሁፍ ማውጣት

መርጃ ቁጥር 5 - በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችን የሚመልስ እውነታውን ማሳያ ጽሑፍ

መርጃ ቁጥር 6 - ንግግሮች (ለአውደ ጥናት፣ ለጉባኤ፣ ለኮንፍረንስ የተዘጋጁ)

መርጃ ቁጥር 7 - ለመገናኛ ብዙሃን የሚሰጥ የሰነድ መያዣ (press kits)

## መልዕክተኛ መምረጥ

የአድቮከሲ ሥራውን ለመሥራት የሚረዱት ከላይ መሣሪያዎች በማለት የጠቀስናቸው አጋዦች ከተዘጋጁ በኋላ መልዕክቱ እንዲተላለፍለት ለሚፈለገው ወገን ማን ያድርሰው? የሚለውን ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚሁም ጋር ምንድ ነው የተባለው? እንዴት ነው የተባለው? የሚሉት ነጥቦችም እንዲሁ ጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ትክክለኛውን መልዕክተኛ መምረጥ የአድቮከሲውን ሥራ ውጤታማ ሊያደርገው ወይንም ሊያከሽፈው ይችላል፡፡

በመሠረቱ መልዕክተኛው፡-

- መደበኛ በሆኑና መደበኛ ባልሆኑ የንግግር ሥርዓቶች የተካነ ተናጋሪ መሆን አለበት፣
- በጉዳዩ ላይ በቂ እውቀት ያለው መሆን አለበት፡፡ በጥያቄ ላይ ባሉ ነጥቦች ዙሪያም በቂ ልምድ ያለው ቢሆን ተመራጭ ነው፡፡

የተዘጋጀውን ጽሑፍ የሚወስደው ሰው መልዕክቱን በሚያደርስባቸው ሰዎች ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት ያለው ሰው መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ የቀድሞ ፓርላማ አባላትን የወቅቱ የፓርላማ አባላት ዘንድ መላክ ይቻላል፡፡ ኤክስፐርቶችንና የምርምር ሰዎችንም እንደዚሁ አቻዎቻቸው ዘንድ መላክ ይቻላል፡፡

## በድርጊት ላይ ያሉ ነጥቦች ላይ ለውጥ ማምጫ መንገዶች

አሁን በምን ዓይነት መርጃ መሣሪያዎች ማን ላይ ተፅእኖ ማድረግ እንዳለብን አውቀናል፡፡ የሚቀጥለው ሂደት መልዕክቱ ታዳሚው ዘንድ እንዲደርሰ ውጤታማ መንገድን ስለመከተል የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በታች በቀረበው መልክ ልትጠቀሙባቸው የምትችሉ መርጃ መሣሪያዎች ተዘርዝረዋል፡፡ መርጃ መሣሪያዎቹ በግለሰቦች፣ በድርጅቶች ወይንም በፖሊሲ አውጭዎች ፣ በሕግ አውጪዎች ወይንም በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የአድቮከሲ ሥራ፣ ሰነዶችና ክህሎቱ ተጽእኖ እንዲያሳድሩ የሚያስችሉ ሲሆኑ፣ የነዚህን ወገኖች ድጋፍ ለማግኘ ትም የሚረዱ ናቸው፡፡ እነዚህ መርጃዎችም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡

- መርጃ ቁጥር 8 የማኅበሩን አባላት ስለማስተማርና የአድቮከሲ ሠራተኞች እንዲሆኑም ስለመመልመል
- መርጃ ቁጥር 9 መሰረታዊ የሆኑ አውታሮችን ማንቀሳቀስ
- መርጃ ቁጥር 10 የሕዝብን አመለካከት ከመቅረጽ አንጻር ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ስለመሥራት
- መርጃ ቁጥር 11 የፖሊሲ አውጪዎችን፣ ሕግ አውጪዎችን፣ አስተዳዳሪዎችንና የእነርሱን ሠራተኞች ድጋፍና ከበሬታን ስለማግኘት፣
- መርጃ ቁጥር 12 የተዋጣለትን ቅንጅት መፍጠር፣

- መርጃ ቁጥር 13 ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳን እንዴት እንደሚዘጋጀና የአድበቮከሲ ሥራ እንደሚሠራበት፣
- መርጃ ቁጥር 14 የተዋጣለት የሕግ ምክር አገልግሎት ፕሮግራም እንዴት መቅረጽና መተግበር እንደሚቻል የሚሉ ናቸው::

የማኅበሩ አባላት እነዚህ የተዘረዘሩትን መርጃዎች በሙሉ በመመልከት የትኛው መርጃ መሳሪያ የማኀበራቸው የአድቮከሲ ሥራ ግቡን እንዲመታ እንደሚያስችል መወሰን አለባቸው:: እነዚህ መርጃ መሣሪያዎች የማኅበሩን አጠቃላይ እቅድ ወይንም የአድቮከሲ ሥራ እቅድ ለመንደፍ የሚያስችሉ ጠቃሚ ነጥቦች እንደሆኑ ማወቅ ያስፈልጋል:: መርጃ መሣሪያዎቹም ከዚህ በታች አንድ በአንድ በዝርዝር ቀርበዋል::

## *መርጃ ቁጥር 8፡ የማኅበሩን አባላት ስለማስተማርና የአድቮከሲ ሠራተኛ እንዲሆኑም ስለመመልመል*

የማኅበር አባላት ማኅበራቸው በምን ጉዳይ ላይ እና ለምን የአድቮከሲ ሥራ እየሠራ እንደሚገኝ ማወቅ ይፈልጋሉ:: ለምትሠሩት የአድቮከሲ ሥራም እነርሱም ሆኑ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ወገኖች አጋዥ ኃይል ሊሆኑላችሁ ይችላሉ:: እዚህ ላይ መሥራት የሚገባችሁ የመጀመሪያው ነገር የማኅበራችሁን አባላት በምን ጉዳይ ላይ የአድቮከሲ ሥራ እንደሚሠራና ለምንስ ያ አድቮከሲ እንደሚያስፈልግ ማስተማር ነው:: ለዚህም ሲባል ወቅቱን ጠብቆ በሚቀርብ የሥራ ሪፖርትና በማኅበሩ እትሞች ላይ ስለጉዳዩ ገለጻ መስጠት አስፈላጊ ነው::

በደረጃ ሁለት ላይ በተመለከተው መሠረት ያለውን ከፖሊሲ ጋር የተያያዘ ችግር አስመልክቶ ለአባላት የቀረበውን የጥናት መጠይቅ ውጤት ጠቅለል አድርጐ ማቅረብ ሥራውን ለመጀመር መንደርደሪያ ይሆናል:: ይህ አባላት እንዲያዩት የተደረገው የመጠይቅ ውጤት የአድቮከሲ ሥራን ለመሥራት የተመረጠው ነጥብ ላይ የእነርሱ ተሳትፎ እንዳለበት ያሳያቸዋል:: ቀጥሎም ከላይ በደረጃ ቁጥር ሁለት ላይ እንደተገለፀው ጉዳዩን አስመልክቶ የተዘጋጀው አጭር መግለጫ ከእያንዳንዱ አንገብጋቢ ነው ተብሎ ከተመረጠው ነጥብ ጋር አብሮ ይቀርባል:: ይህም ጉዳዩ ለምን አንገብጋቢ እንደሆነና ፖሊሲውን አስመልክቶም የማህበሩ አቋም ምን እንደሚመስል ለአባላቱ ለማሳየት ይረዳል:: ለዚህ ጉዳይ ከላይ በመርጃ መሣሪያነት ከተጠቀሱት ውስጥ እንደ እውነታ ማሳያ እና እንደ የአቋም መግለጫ ማሳያ የመሳሰሉት ጽሁፎች አብረው ከቀረቡ ሰነዱ ራሱ ምንን መሠረት እንዳደረገ በግልጽ ያሳያል:: የአድቮከሲ ሥራ ሰነዶችን በማኅበሩ ድረ ገጽ ላይ ማሰራጨት ሰነዱን በቀላሉና በአነስተኛ ወጪ አንባቢ ዘንድ እንዲደርስ ለማድረግ ይረዳል:: አባለትም የአማካሪ ኮሚቴውን ሠራተኞች በማግኘት እገዛ እንዲሰጡ መጠየቅ አለባቸው::

የማኅበሩ አባላት አንድ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ ካገኙ በኋላ የሚሠራውን የአድቮከሲ ሥራ ለማጠናከር በእነርሱ ወገን ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ማሳወቅ አለባቸው:: የአማካሪ ኮሜቴው ሠራተኞች ሴሚናሮችን አዘጋጅተው አባላትን በመጋበዝ፣ በዚያው መድረክ ፖሊሲ የመቅረጽ ሂደት እንዴት እንደሚሠራ፣ የእነርሱ ድጋፍ ለምን ወሳኝ እንደሆነና እንዴት በአግባቡ ድጋፍ ሊሰጡ እንደሚችሉ ገለጻ ማድረግ አለባቸው:: የአባላትን ድጋፍ የመጠቀሙ ሁኔታ ማኅበሩ በመረጠው የአድቮከሲ ስልት ላይ ሊመሰረት ይገባዋል:: አባላትም ይህንን ሥልት በመጠቀም መድረስ የሚገባቸው ታዳሚያቸው ላይ ለመድረስ መንቀሳቀስ አለባቸው:: ይህም አባላት የሚከተሉት እንዲያደርጉ መጠየቅን ያካትታል::

- ነጥቡ ወይንም የአድቮከሲ ሥራ የሚሠራበት ጉዳይ ለምን ጠቃሚ እንደሆነና ምን ዓይነት የአድቮከሲ ድርጊት እየተከናወነ እንደሚገኝ ለሌሎች ወገኖች ገለጻ እንዲሰጡ ማድረግ (ለማያውቋቸው የመንግሥትና የመገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ለሠራተኞች ፣ በሌላ ድርጅት ለሚገኙ ባልደረቦቻቸው ፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለሌሎች)
- ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የመንግሥት ተወካዮችና ለፖሊስ አውጪዎች ደብዳቤ እንዲጽፉ ፣ ፋክስ እና ኢሜል እንዲልኩ፣
- ለፖሊሲ አውጪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት ስልክ እንዲደውሉ፣
- ፖሊሲ አውጪዎችንና የመንግሥት ኃላፊዎችን በግንባር ተገኝተው እንዲያነጋግሩ፣ በማኅበራዊ ዝግጅቶች ወይንም በአድቮከሲ ኮሚቴው ወይንም በሌሎች ወገኖች በተዘጋጁ መድረኮች ለይ እንዲገኙ:: (በእነዚህ ዝግጅቶች ላይ እውነታ የሚያሳየውን ጽሑፍ ወይንም ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ጽሁፎችን ይዞ መገኘትና ማሠራጨት መልካም አጋጣሚ ነው::)

## መርጃ ቁጥር 9: መሠረታዊ የሆኑ አውታሮችን ስለማንቀሳቀስ

በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ አውታሮች ወይንም ቡድኖች የሚባሉት የጋራ ተስፋ፣ ዓላማ እና የሚጋሩት ፍርሀት ስላላቸው አንድ የሆኑ ግለሰቦች ስብስቦች ናቸው:: እነዚህ ወገኖች በአንድ ጉዳይ ላይ አንድ አቋም በመያዝና ይኼንኑ አቋማቸውን በማንገብም በፖለቲካዊ ሥርዓት ውስጥ የሚሳተፉ ናቸው:: እነዚህ ወገኖች ዲሞክራሲያዊ በሆነ ማኅበረሰብ ውስጥ ድጋፍ ያለው ተሳትፎ ለማካሄድም ወሳኝ ኃይል አላቸው::

ከአሜሪካን አብዮት በኋላ ዴሞክራሲ በአማሪካን አገር ወዲያውኑ ግቡን እንዲመታ ካስቻሉ ምክንያቶች መካከል አንዱ የዜጐችን ጉዳዮች በፖሊሲ አውጪዎች ዘንድ ወክለው የሚቆሙ ማህበራት ሀብት መኖሩ እንደነበረ የ19ኛው መቶ አመት እውቁ የዴሞክራሲ አቀንቃኝ አሌክሲስ ዲቶኩዊቬለ ይናገራል::

ማኅበራት እነዚህን አካላት ማንቀሳቀስ የሚገባቸው በራሳቸው ሥር ከሚገኙት ጀምረው ነው፡፡ እነዚህም ወገኖች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የማኅበሩ አባል ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችና  በጡረታ የተገለሉ ሠራተኞች፣
- የማኅበሩ አባላት ሽሪኮች፣
- የራሱ የማኅበሩና የአባላቱ እቃ አቅራቢዎች፣
- በጡረታ ላይ የሚገኙ የማኅበሩ አባላት፣
- የማኅበሩ አባላት ደንበኞች፣
- የቤተሰብ አባላት እና
- ከማኅበሩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች፡፡

የአድቮከሲ ኮሚቴው ቅጥር ሠራተኞች ከነዚህም በተጨማሪ በዚያው የአድቮከሲ ሥራ በሚሠራበት ጉዳይ ላይ ፍላጐት ያላቸውንና ነገሩ የሚመለከታቸውን ቡድኖች ወይንም ግለሰቦች ድጋፍ ማሰባሰብም አለባቸው፡፡ ይህ የማሰባሰቡ ሂደትም የሙያ ማኅበራትን፣ የሸማቾች ቡድንን ተማሪዎችንና የኅብረተሰቡን አካላት ያካትታል፡፡

የማኅበሩ አባላትና የአድቮከሲ ኮሚቴው ሠራተኞች የተዘጋጁትን የአድቮከሲ መርጃ መሳሪያዎች ወይንም ጹሑፎች እነዚህን ከላይ ያነሳናቸውን ወገኖች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ብሎም ከጐን ለማሰለፍ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ ግንዛቤ የማስጨበጡና ከጐን የማሰለፉን ሥራ ሠራተኞቹ ስልክ በመደወል፣ ኢሜል በማድረግ ወይንም ገለፃ በሚሰጡባቸው መድረኮች እና በቁርስ ወይንም በምሳ ወይንም በእራት ግብዣ ፕሮግራሞች ላይ እንዲገኙ በመጋበዝ ሊሠሩት ይችላሉ፡፡ አሁንም ለዚህኛው ወገን የሚተላለፈው መልዕክት እና መልክቱን የሚያስተላልፈው ሰው ለእነርሱ በሚስማማ መልኩ መዘጋጀት አለበት፡፡ በእያንዳንዱ ጉዳይ ጋባዡ ወገን ፡-

- ጉዳዩ ለእነርሱም ለምን አስፈላጊ እንደሚሆን፣
- በዚያ ጉዳይ ላይ የተወሰደው አቋም ምን እንደሆነ እና
- ጉዳዩ ላይ ድጋፍ ለመስጠት ከእነርሱ ምን እንደሚጠበቅ በሚገባ ግንዛቤ ማስጨበጥ አለበት፡፡

ይህ ከተደረገ በኋላ በየአድቮከሲ ኮሚቴው ሠራተኞች ከእነዚህ ወገኖች መካከል የማኅበሩን አቋም የደገፉትን ግለሰቦችና ድርጅቶች ስም እንዲሁም ሙሉ አድራሻቸውን መዝግበው መያዝ አለባቸው፡፡ ይህንን ማድረግ እነዚህን ግለሰቦችና ቡድኖች ጉዳዩን አስመልክቶ የተከሰተ አዲስ ነገር ካለ ለማሳወቅ፣ ስምምነት ላይ የተደረሰበትን የአድቮከሲ ሥራ ለመከታተል፣ ለፖሊስ አውጪዎች ጉዳዩ ምን ያህል ደጋፊዎች እንዳሉት ለማሳየት፣ እንዲሁም ጥሩ የግንኙነት መረብ ለመዘርጋትና ይኼንኑም ግንኙነት በመጠቀም እነዚህን ወገኖች ከክርክር መድረክ በፊት ለሚሠሩ ከፍተኛ የአድቮከሲ ሥራዎች ወይንም ለድምጽ አሰጣጥ ወይንም የሕዝብ አስተያየትን አቅጣጫ ለማስያዝ በሚያስፈልግበት ጊዜ ለመጠቀም ይረዳል፡፡

## መርጃ ቁጥር 10፡ የሕዝብን አመለካከት ከመቅረጽ አንጻር ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ስለመሥራት

የመንግሥት ኃላፊዎችንና ፖሊሲ አውጪዎችን ከማግኘት በፊት የሕዝብን አመለካከት ከማኅበራት ፍላጐት አንጻር መስመር ማስያዝና ማሰባሰብ ለአድቮከሲ ዘመቻ ማሳካት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ይኸንንም ለማከናወን ተመራጩ መንገድ መገናኛ ብዙሃንን ማሰባሰብ ነው፡፡ ያለክፍያ ጉዳዩ ዜና ስለሆነ ብቻ የሚሠሩ እና በክፍያ የሚሠሩ ሁለት ዓይነት የዜና ሽፋኖች ወይንም መገንኛ ብዙሃን አሉ፡፡

ያለክፍያ የዜና ሽፋን የሚሠሩት መገናኛ ብዙሃን ለጉዳዩ የዜና ሽፋን የሚሰጡት ነጥቡ የዜና ይዘት ያለው በመሆኑ ነው፡፡ በእነዚህ መገናኛ ብዙሀን ተጠቅሞ አስተማማኝ የሆኑ ጽሑፎችን በማቅረብ፣ ለአዘጋጆች የሚጻፉ ደብዳቤዎች በሚተላለፍበት ገጻቸው ወይንም ፕሮግራማቸው በመጠቀም፣ ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲደርሳቸው በማድረግ እንዲሁም ሌሎች መንገዶችን ጭምር በመጠቀም ጥያቄ ስለተነሳበት ነጥብ ወይንም ስለማኅበሩ እንቅስቃሴ (ስብሰባዎች፣ አውደ ጥናቶችና ወርክሾፖች) መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ እነዚህ መገናኛ ብዙሃን በማስታወቂያ መልክ የማይተላለፉ በመሆናቸው ተአማኒነታቸውም የጐላ ነው፡፡

በመሆኑም የዚህ ዓይነቶቹን መገናኛ ብዙሃን መመልመልና ከጐን ማሰለፍ ማኅበራት ከፖሊሲ ጋር የተያያዙ ችግሮችን አስመልክቶ በያዙት አቋም ከሕዝብ ድጋፍ እንዲቸራቸው ለማስቻል ወሳኝ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ ከአድቮከሲ ሠራተኞቹ መካከል አንዱን በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ከመገናኛ ብዙሃኑ ጋር ጥሩ ግንኙነት የመፍጠሪያ ስልት እንዲቀርጽና እንዲተገብር መመደብ ይመከራል፡፡ ይህም ግለሰቡ የሚከተሉት ችሎታዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

- ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የመሥራት ልምድ ያለው፣
- ጥሩ የጽሑፍና የንግግር ችሎታ ያለው፣
- ከተለያዩ ሰዎች ጋር የመግባባት ብቃት ያለው፣
- ፖሊሲ በማውጣት ሂደት ላይ የጠራ እውቀት ያለው፣
- የአድቮከሲ ሥራ በሚሠራበት ጉዳይ ላይ በቂ ግንዛቤ ያለው፣
- ከመንግሥት ኃላፊዎችና ከእነርሱ ሠራተኞች እንዲሁም ከመሰል ማኅበራት ጋር ጥሩ የሥራ ግነኙነት ያለው፡፡

ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ግንኙነት የመፍጠሩን ሥራ እንዲሠራ የተመደበው ሰው የሚጠበቀውን ውጤት ከማሳደግ አንጻር ከሌሎቹ የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በቅርበት መሥራት አለበት፡፡ የተቀሩት የአድቮከሲ ኮሚቴው ሠራተኞች ክንውኖችን አስመልክቶ ለዚህ ባለሙያ ቀድመው ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ ቁልፍ ስለሆኑ ታሣታፊዎችና ጉዳዩን ስለተቀበሉት ወገኖች እና በጉዳዩ ላይ የመገናኛ ብዙሃንን ሽፋን እና የሕዝብ አመለካከትን

ስለሚያስተጓጉሉ ወቅታዊ ጉዳዮች በየጊዜው ሊያሳውቁት ይገባል። የዚህ ዓይነቱን መረጃ በወቅቱ ማግኘት የመገናኛ ብዙሃን ግንኙነትን አስመልክቶ የሚከናወኑ ተግባራትን ለማቀድ ይረዳል። ይህም ተግባር መገናኛ ብዙሃንን በአንድ ቁልፍ ጉዳይ ላይ ቀድሞ መጋበዝን (አስፈላጊ ሲሆንም ሌሎች ቡድኖችን ጭምር)፣ ለመገናኛ ብዙሃን የሚላኩ ሰነዶችን የሚይዘውን ሰነድ መያዣ (press kit) ለመገናኛ ብዙሃን አባላት መላክን ያካትታል። ይኸው ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የሚሠራው ባለሙያ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን ለመገናኛ ብዙሃን የሚላኩትን እንደ እውነታ ማሳያ ጽሑፍ ፣ አጠቃላይ መረጃ እና ሌሎችንም ሰነዶች ማዘጋጀት አለበት።

የመገናኛ ብዙሃን ግንኙነት ባለሙያው ከመገናኛ ብዙሃንና ከሌሎች ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር ጥሩ የሆነ የሥራ ግንኙነት መመሥረት አለበት። ይህም ማለት እነዚህን ወገኖች ከሁሉም በላይ ዝግጅቶች ላይ እንዲገኙ ማድረግን እና የአድቮከሲ ሥራ እየተሠራበት ካለው ነጥብ ጋር ግንኙነት ስላላቸው ዝግጅቶች ቀረቤታ እንዲኖራቸው ማድረግን እና እውነታውን እንዲረዱ ማድረግን ያካትታል። ለምሳሌ ያህልም የአድቮከሲ ሥራ እየተሠራበት ያለውን ነጥብ ወይንም እነዚህን ወገኖች የሚደግፍ ወይንም የሚቃወም አዲስ ሃሳብ ሲመጣ ወይንም የማኅበሩን ነጥብ የሚደግፍ አዲስ እውነታ ሲከሰት ማሳወቅ የዚሁ ባለሙያ ተግባር ነው። የማሣወቁ ሂደትም በስልክ፣ በኢሜል ወይንም በፋክስ ሊከናወን ይችላል። እያንዳንዱ ግንኙነትም በጉዳዩ ላይ ብቻ ያተኮረ፣ አጭርና ግልጽ መሆን አለበት።

በነጥቡ ላይ በቂ የሆነ የሕዝብ ድጋፍ ተገኝቶ ከሆነ ያለ ክፍያ የዜና ሽፋን የሚሰጡትንና ተአማኒ የሆኑትን መገናኛ ብዙሃን መጠቀም በቂ ነው፡ ይህ ካልሆነ ግን በክፍያ የሚያስተላልፉትን መገናኛ ብዙሃን መጠቀም አግባብ ነው። የክፍያ መገናኛ ዘዴዎች የሚባሉት በቴሌቪዥን ፣ በሬዲዮ፣ በጋዜጣ እንዲሁም በቢልቦርድ፣ በባነርና በመሳሰሉት ከቤት ውጪ በሚለጠፉ መገናኛ ዘዴዎች ማስታወቂያ የሚያስተላልፉ የህዝብ መገናኛ ዘዴዎች ናቸው። እነዚህ በክፍያ የሚሠሩት መገናኛ ብዙሃን በዋጋቸው ወደድ ስለሚሉ ጥበብን መጠቀም ያስፈልጋል።

የመገናኛ ብዙሃኑን ግንኙነት የሚሠራው ባለሙያ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመመካከር መልዕክቱ ሊደርሳቸው የሚገባውን ውስን ታዳሚዎች እና እነዚሁ ወገኖች መልዕክቱን የሚያደምጡበትን ትክክለኛውን የክፍያ መገናኛ ብዙሃንና ሠአታቸውን መለየት አለበት። ይህንን በማድረጉም መልዕክቱን በትክክል የሚፈለገው ወገን ጋ ለማድረስና የሚወጣውንም ወጪ በአግባቡ ተጠቅሞ የታለመውን ግብ ለመምታት ያስችለዋል።

በደረጃ ሁለት ላይ በተጠቀሰው መሠረት የጥናት ውጤቶች እና የተሰባሰቡ የሕዝብ አስተያየቶች መልዕክቱ የሚተላለፍለትን ትክክለኛውን ታዳሚ ለመምረጥ ይረዳሉ። መልዕክቱን የመቅረጹ ሂደት የአድቮከሲ ልምድ ያለውን የመገናኛ ብዙሃን ወይንም የማስታወቂያ ባለሙያ የመቅጠር ሁኔታ ሊጠይቅ ይችላል። በየትኛውም መልኩ ቢሆን ግን የሚተላለፈው መልዕክት አጭር፣ ግልጽና ድጋፍን የሚያስገኝ መሆን አለበት። የመገናኛ ብዙሃን ግንኙነት ባለሙያው

ከዚህም በተጨማሪ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ማስታወቂያው የሚተላለፍበትን የጊዜ ሰሌዳ ማውጣት አለበት፡፡

## መርጃ ቁጥር 11፡ የፖሊሲ እና የሕግ አውጪዎችን፣ የአስተዳዳሪዎችን እና የእነርሱን ባልደረቦች ድጋፍና ከበሬታ ስለማግኘት

ለማኅበራት የአድቮከሲ ሥራን የመሥራት ዋነኛው ዓላማ ፖሊሲ በማውጣት ሂደት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን በመደበኛነት ከእነርሱ ፍላጐት ጋር የሚጣጣሙ ፖሊሲዎችን ፣ ሕጐችን፣ ደንቦችን ማስፈን ነው፡፡ ይህም ከፖሊሲና ሕግ አውጪዎች እንዲሁም ከእነርሱ ባልደረቦች ጋር (ለግንኙነት የሚያስፈልጉት ሰዎች ከጉዳይ ጉዳይ ይለያያሉ) ጥሩ የሥራ ግንኙነትን መፍጠርን ያካትታል፡፡ የኮሚቴው ሠራተኞች ለመንግሥት ባለሥልጣናቱ ጉዳዩን አስመልክቶ አንኳር መረጃ በመስጠት አመለካከታቸውን እንዲቀይሩ ማድረግ አለባቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኙ አስተዳዳሪዎችና ሠራተኞች ነጥቡን አንዴ እንዲደግፉ ከተደረገ የመንግሥት ለውጥ እስኪመጣ ድረስ የያዙትን አቋም እንደያዙ ሊዘልቁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የአድቮከሲ ኮሚቴ ሠራተኞች ከእነዚህ መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ጋር ጥሩ የሥራ ግንኙነት መፍጠር አለባቸው፡፡

ተደጋጋሚና ውጤታማ የሆነ ግንኙነት ለውጤታማ ትስስር መሠረት ነው፡፡ ከዚህ የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ የንግድ ማኅበራት ከፖሊሲ አውጪዎችና ሠራተኞቻቸው ጋር ጤናማ የሥራ ግንኙነት መመሥረት ይችላሉ፡፡

(አሁንም፣ ትክክለኛው ቅደም ተከተልና የሚወሰደው እርምጃ እያንዳንዱን ጉዳይ አስመልክቶ በሚነደፈው እቅድ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል፡፡)

- ከአንድ ከተወሰነ ፖሊሲ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ላይ ማኅበሩ የወሰዳቸውን አቋሞች የሚገልጹ መርጃዎችን በማዘጋጀት ለመንግሥት የቢሮ ኃላፊነት ከታጩ ሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር፡፡ በዚህ ወቅት የማኅበሩን አባላት ቁጥርና ማኅበሩ የያዘውን አቋም የሚደግፉ ሰዎች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ መግለጽ አስፈላጊ ነው፡፡ እዚህ ላይ እውነታ ማሳያ ጹሑፎችንና አጫጭር መግለጫዎችን መጠቀም ግለሰቦቹን ወደማኅበሩ ነጥብ ለመውሰድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እጩዎቹ በሚያነሷቸው ነጥቦች ላይ የማኅበሩን አቋም ለሕዝብ እንዲያንፀባርቁና እንዲያነሱት መገፋፋት ያስፈልጋል፡፡
- ከምርጫ በኋላ በምርጫው ያሸነፉትን ኃላፊዎችና የእነርሱን ቢሮ ሠራተኞች ገለጻ በሚሰጥባቸው መድረኮች፣ በማኅበራዊ ግንኙነቶች ፣ በቁርስ፣ በምሳና በእራት ግብዣዎች ላይ እንዲገኙ በመጋበዝ፣ ማኅበሩ በሚያነሣው ጥያቄ ላይ የተያዘውን አቋም እና አጠቃላይ ዓላማውን ማብራራትና ከማኅበሩ አባላትና ደጋፊዎች ጋር እንዲገናኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- የፖሊሲና ሕግ አውጪዎችን አጀንዳ በመደበኛነት መከታተል አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን በማድረጉም ማኅበሩ በፖሊሲ ክርክሮችና ድምጽ በሚሰማባቸው መድረኮች ላይ አቋሙን በወቅቱ እንዲያሳውቅ ይረዳዋል፡፡ እዚህም ላይ ከላይ የአድቮከሲ ሥራ ሰነዶች ስንል የዘረዘርናቸውን መጠቀም ለውጥ ከማምጣት አንጻር ጠቃሚ ነው፡፡
- ፖሊሲና ሕግ አውጪዎችን እንዲሁም ሕግ አስፈጻሚዎችንና የእነርሱን ቢሮዎች ሠራተኞች በሚነሣው ነጥብ ዙሪያ ገለጻ በሚደረግባቸው መድረኮችና በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይቶች ላይ እንዲገኙ በተደጋጋሚ በመጋበዝ ጉዳዩ ከጭንቅላታቸው እንዳይወጣ ለማድረግ ይቻላል፡፡
- የሕግና ፖሊሲ አውጪዎችን ንግግሮችና የምርጫ ውጤቶቻቸውን ማሰባሰብና ይኸም እየተደረገ እንደሚገኝ ለእነርሱ ማሳወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ ንግግሩንና የምርጫ ውጤቱን በማሳተም ለማኅበሩ አባላት፣ ለመሠረታዊ አውታሮች እና ፍላጐት ላላቸው ማኅበራት ማሠራጨት ያስፈልጋል፡፡ እውነታውን ብቻ በሚያሳይ መልኩ በአጭሩ ማዘጋጀትና ይህንንም ታዳሚያን ዘንድ ለማድረስ ፋክስና ኢሜልን በመሳሰሉት ዘመናዊ የግንኙነት መንገዶች መጠቀም ወጪን ከመቆጠቡ ባሻገር በሠዐቱ ለማድረስም አዋጪ ነው፡፡
- የሚወጡ ሕጐችን አስመልክቶ መረጃ መያዝ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ ጉዳዩ ለቋሚ ኮሚቴ ውይይት መቼ እንደተላከ፣ በጉዳዩ ላይ የሚደረገው ውይይት መቼ ሊደረግ እንደታቀደ  እና የመሳሰሉትን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ይኸንንም መረጃ በመያዝና ከሕግ አውጪው ጋር የሚሠሩ ሠራተኞችን ግንኙነት በመጠቀም በታዛቢነት ወይንም በሚደረገው ውይይት ላይ በተሳታፊነት ወይንም በአስረጂነት ሊገኝ የሚችል አንድ ልዑክ አዘጋጅቶ መላክ ይቻላል፡፡
- በምስክርነት እንድትገኙ ከተጠየቀ ትክክለኛውን አካሄድ ማወቅና የርሱንም ቅደም ተከተል መገንዘብ  ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ጉዳይ እውቀት ያላቸው፣ የሚከበሩና ጥሩ የንግግር ችሎታ ያላቸውን ሰዎች በመምረጥ ጉዳዩን በአጭሩ እንዲያስረዱና በዚያም ላይ የማኅበሩ አቋም ምን እንደሚመስል እንዲያመላክቱ መላክ የሚወጣው ሕግ ወይንም መመሪያ ምን ያክል ዋነኞቹን ባለድሪሻዎች እንደሚነካ ለማሳየት ያስችላል፡፡ የሚቀርበውን ገለጻ አጠርና ጠቅለል በማድረግ ለጥያቄና መልሱ ክፍለ ጊዜ በቂ ሰአት መተው ያስፈልጋል፡፡ ረዥም፣ አሰልቺና አላስፈላጊ ዝርዝሮችን ማስወገድም አስፈላጊ ነው፡፡
- ማኅበሩን ከአንድ ከተወሰነ ፓርቲ ጋር ማገናኘት አያስፈልግም፡፡ ነገር ግን ማኅበሩ የሚያራምደውን አቋም ከሚደግፉ የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር ወዳጅ መሆኑን ማሳወቅ ይቻላል፡፡
- የፖሊሲ አውጪዎች መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ጠቃሚ ሆነው ሲገኙ ግልባጩን ለአለቆቻቸው በማድረግ በስማቸው የምስጋና ደብዳቤ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡

- ፓርላማው በሥራ ዘመን ላይ በሚገኝበት ወቅት ፖሊሲ አውጪዎችንና የእነርሱን ሠራተኞች ምሳ ላይ በማግኘት ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየት ጠቃሚ ነው፡፡
- ፖሊሲ አውጪዎችን እውቅና የሚያጐናጽፍ እና በክብር እንግድነት እንዲገኙበት የሚያደርግ ግብዣ ምሳ ወይንም ሌላ ልዩ ዝግጅት ማድረግና በዚያው ሥነ ሥርዓት ላይ ቁልፍ የሆኑ የማኅበሩን አባላት እና የማኅበራት አቋም የሚደግፉ የሌሎች ማኅበራትን ተወካዮች መጋበዝ፡፡ በዚሁ ወቅት ፖሊሲ አውጪዎች ጉዳዩን አስመልክቶ የሰጡትን ድጋፍና የሠሩትን ሥራ የሚያሞግስ ጋዜጣዊ መግለጫ ማሠራጨት ያስፈልጋል፡፡
- በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ በብሔራዊ፣ በክልልና በክፍለ ከተማ የመንግሥት ተወካዮች ፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የሕግ አውጪ ተቋማት ኃላፊዎች ሆነው እርስ በርሳቸው የሥራ ግንኙነት የሌላቸውን ቁልፍ የሆኑ ተዋናዮችን የሚያገናኝ ስብሰባ ማዘጋጀት፡፡
- በማኅበሩ ጉዳይና የአድቮከሲ ሥራ ጥረት በተደረገበት ላይ ድጋፋቸውን የሰጡትን ሁሉ በስም ማመስገን ያስፈልጋል፡፡

## መርጃ ቁጥር 12

## የተዋጣለት ቅንጅት ስለመፍጠር

በአንድ ወይንም በተለያዩ ማኅበሩ በሚወስዳቸው አቋሞች ላይ ድጋፋቸውን የሚሰጡ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ቁጥር ለማብዛት ቅንጅትን መፍጠር ጠቃሚ መንገድ ነው፡፡ ብዙ ድምጽ ሰጪዎች ማኅበሩ የያዘውን አቋም ደገፉ ማለት ፖሊሲ አውጪዎች ለጉዳዩ ጆሮአቸውን ሰጡ ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ቁጥርን ማብዛት ጥንካሬ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ቅንጅት መፍጠር የአድቮከሲ ሥራ እንቅስቃሴያችሁን የሚታይና ተአማኒነት ያለው ያደርገዋል፡፡ በተለይ አንድ የተወሰነ ፖሊሲን፣ አዋጅን ወይንም ደንብን ከመለወጥ አንጻር የማኅበር አባላት ቁጥር አነስተኛ ሆኖ ሲገኝ እና በርካታ ቁጥር ያለውን ድጋፍ ማሰባሰብ ሲያስፈልግ በማኅበራት መካከል ቅንጅት መፍጠር እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ቀድሞ የተሰበሰበውን መረጃ በመጠቀም ማኅበሩ የያዘውን አቋም የሚደግፉትን ማኅበራት መሪዎች ማነጋገር እና ድርጅቱ በተወሰነ ወይንም ጥቅል በሆነ ጉዳይ ላይ ቅንጅት መፍጠር የሚፈልግ መሆን አለመሆኑን መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ጊዜ የቅንጅቱ አባላት ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡትን ካነጋገራችሁ በኋላ የእያንዳንዱ ድርጅት ተወካዮች የሚሳተፉበት ስብሰባ አዘጋጁ፡፡

በስብሰባው ወቅት እያንዳንዱ ድርጅት ቅንጅቱ በሚያካሂደው እንቅስቃሴ ላይ በምን ያህል መጠን ተሳታፊ ሊሆን ፍቃደኛ እንደሆነ ማመላከት አለበት፡፡ የቅንጅቱ ይዘት ቅንጅት

በተፈጠረበት ጉዳይና እያንዳንዱ የቅንጅቱ አባል ሊሰጥ በተዘጋጀው ትኩረት ላይ የሚወስን ነው:: አንዳንዶቹ የቅንጅቱ አባላት ምንአልባት በከፍተኛ ሁኔታ መንቀሳቀስ የሚፈልጉ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ በመጠነኛ ሁኔታ መሳተፍ የሚፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ:: በዚህ መረጃ ላይ በመንተራስም የቅንጅቱ አባላት ከዚህ በሚከተለው ላይ መስማማት ይገባቸዋል::

- ስለቅንጀቱ የእዝ ጠገግ
- ስለሥራ ክፍፍል
- ስለአድቮከሲ ስልትና የጊዜ ሰሌዳ፣ (በደረጃ አምስት ላይ የተመለከተው ስልትና የጊዜ ሰሌዳ ለዚህ እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል)
- ወጪን ስለመጋራት፣
- የቅንጅቱን ቃል አቀባይ ስለመወከል፣
- ስለቅንጅቱ አስተባባሪ እና
- ስለጋራ መልዕክት:: (በወቅታዊው እውነታና ጥናት ላይ ተመስርቶ ተመሣሣይ እና አንድ ወጥ አቋም ለመያዝ ከደረጃ አንድ እስከ ሰባት በተዘረዘሩት የአድቮከሲ መርጃ ሰነዶች መጠቀም ጠቃሚ ነው:: የጋራ የሆነ አቋም ለማምጣት ምንአልባት ቅንጅቱን ያስተባበረው ማኅበርን መጠነኛ የአቋም ለውጥ እንዲያደርግ ሊያስገድደው ይችላል:: ጉዳዩ ከመጽደቁ በፊት ግን ማስተካከያ የተደረገበት አቋም ከማኅበሩ ዓላማና ግብ ጋራ የተጣጣመ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል::

የዚህ አይነት እርምጃ የቅንጅቱ አባላት አንድ ወጥ የሆነ ድምጽ እንዲኖራቸውና ውጤታቸውም ከፍተኛ እንዲሆን ይረዳል::

የቅንጅቱ አስተባባሪ ከቅንጅቱ አባላት ጋር በመደበኛ ሁኔታ በመገናኘት ከቅንጅቱ ተግባር እና ዓላማ አንጻር የቅንጅቱን እንቅስቃሴ የሚደገፉ ዝግጀቶችን እንደዚሁም ያሉ ለውጦችንና ሌሎች ጉዳዮችን ማሳወቅ አለበት:: አስተባባሪው ጠቃሚ የሕዝብ አስተያየት መስሚያ መድረኮች፣ ክርክሮችና ጉባኤዎች ሲኖሩ ከወቅቱ ቀደም ብሎ ለአባላት ማሳወቅ ይገባዋል:: ይህ በመደረጉም አባላት ጊዜያቸውን በማመቻቸት በእነዚህ ክንውኖች ላይ ለመሳተፍ ይችላሉ:: ከዚህም በላይ በቅንጅቱ አባላት መካከል አንድነትና ቁርጠኝነትን ለመመሥረት ይረዳል::

የቅንጅቱ አስተባባሪ የቅንጅቱ አባል ለመሆን የማይፈልጉ ነገር ግን የቅንጅቱን አቋም ሙሉ ለሙሉ ወይንም በከፊል የሚደግፉ ቡድኖችን ድጋፍም ማሰባሰብ አለበት:: ለእነዚህ ወገኖች በማኅበራችሁ ወይንም በተፈጠረው ቅንጅት የተዘጋጁትን ነጥቦች የሚያሰጨብጡ የአድቮከሲ ሰነዶች መስጠት አለበት:: ይህን ማድረግ እነዚህን ወገኖች በእናንተ አቋም ለይ ያላቸውን ድጋፍ የሚያጠናክር ሲሆን፣ ፖሊሲ አውጪዎችም የነገሩን ክብደት በመረዳት የምታቀርቡትን ሃሳብ ትኩረት ሰጥተው እንዲቀበሉት ያደርጋል::

(የተዋጣለት የቅንጅት አድቮከሲን አስመልክቶ በምሳሌነት የቀረበውን አባሪ ስምንት ይመልከቱ)

## መርጃ ቁጥር 13

## ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ እንዴት እንደሚዘጋጅና እንዴት የአድቮከሲ ሥራ እንደሚሠራበት

በሀገራችሁ የቢዝነስ ሁኔታ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስፈልገውና ይህም ሰፊ ድጋፍ የሚሻ ከሆነ ለዚህ ቁልፍ ዘዴ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ነው፡፡ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ለንግዱ ማኅበረሰብ ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋትና የንግድ እንቅስቃሴዎችን ከማበረታታት ብሎም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከማሳደግ አንጻር ወሳኝ መሣሪያ ነው፡፡ አጀንዳ ቀርጾ ያለውን ኃይል በመጠቀም የንግዱን ኅብረተሰብ ማነቃነቅ በፖሊሲ ጉዳይ ላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሕግና ደንቦች በመቅረጽ ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ይረዳል፡፡

ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ የቢዝነስ እንቅስቃሴ የሚያውኩ ሕግና ደንቦችን ነቅሶ በማውጣት ተጨባጭ የሆኑ አማራጮችን ስንዝሮ ችግሮቹን በማስወገድ የቢዝነስ እንቅስቃሴውን የሚያሳድግ ነው፡፡ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳን ማዘጋጀት የግሉ ዘርፍ ከላይ የተጠቀሰውን ከተገነዘበ በኋላ ያለበትን ችግር እና ስሜቱን በተባበረ ድምጽ ለመንግሥት አካላት ለመግለጽ የሚያችለው ሲሆን፣ የተቀረጸው አጀንዳም ተቀባይነትን እንዲያገኝ ይረዳል፡፡ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ የሥራ ፈጣሪዎችን/ኢንተርፕረነሮችን/ ችግር ከመቅረፍ አንጻር ቁልፍ መሣሪያ እንደሆነ በግብጽ፣ በማላዊ፣ በናይጄሪያ፣ በፓራጓይ፣ በፔሩ፣ በሮማንያና በአሜሪካ በተጨባጭ ታይቷል፡፡

ማንኛውንም የቢዝነስ አጀንዳን ለማዘጋጀት ቁልፉ ጉዳይ የአንድ የተወሰነ ክልልንና የኢንዱስትሪ ፍላጐትን አስመልክቶ ተሳትፎን በማበረታታት የንግዱ ኅብረተሰብ የመጨረሻው ውጤት ባለቤት እንደሚሆን ማሳየት ነው፡፡ የቢዝነስ መሪዎች የተለያዩ በርካታ የቢዝነስ ቡድኖችን በማደራጀትና ቅንጅትን በመፍጠር በአንድ አብይ ጉዳይ ላይ የጋራ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ኃላፊነትን መውሰድ አለባቸው፡፡

የግብጽ የኢንዱስትሪዎች ፌዴሬሽን ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ በሚቀርጽበት ጊዜ የሚከተሉትን ደረጃዎች ተከትሏል፡፡

- ፖሊሲዎችን ማጤንና ይኼንን አስመልክቶ የሚሰጡ አስተያየቶችን ማዘጋጀት፣
- አማራጮች ላይ ለመወያየት ከአባላት ጋር ክፍት የሆነ ስብሰባ ማካሄድ፣
- ከሚመለከታቸው ፓርቲዎች ግብአት ለማግኘት አጀንዳውን በመገናኛ ብዙሃን ማሠራጨት፣
- የፖሊሲ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣

- አጀንዳውን ለሕዝብ ማሳወቅና
- በመንግሥት ሥራ አስፈጻሚና ሕግ አውጪ አካላት ላይ ያነጣጠረ የአድቮከሲ ሥራን መሥራት፡፡

ቅሬታዎችን ለማስወገድ የማኅበራት ነጻነትና በመንግሥት ጉዳይ ላይ የቅሬታ ድጋፎችን የማሰባሰብ መብት ለዲሞክራሲያዊ ተቋማት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ዲሞክራሲ በማደግ ላይ በሚገኝባቸው ቦታዎች ላይም ቢሆን መሠረታዊ የሆኑትን ወገኖች ቅንጅት በመፍጠር እና ለውጥን ለማምጣት አንድ አቋም በመያዝ ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ተችሏል፡፡

ማኅበራት ገበያ መር የሆኑ ፖሊሲዎችን ለማበረታታት ግንባር በሚፈጥሩበት ጊዜ በተናጠል ፖሊሲ ለማስቀየር ከሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ይልቅ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡

የንግድ ማኅበራት እና ሌሎች አንድ ዓይነት ፍላጐት ያላቸው ወገኖች ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ መቅረጽ በሚፈልጉበት ጊዜ ደረጃ በደረጃ ሊከተሉዋቸው የሚገባቸውን መመሪያዎች ለማየት ከፈለጉ በሳይፕ የተዘጋጀውንና በኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት አማካኝነት ወደ አማርኛ የተመለሰውን «ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ መመሪያ»ን መመልከት ይቻላል፡፡

የውጤታማነት ቀመር የሚለው ደግሞ http//www.cipe.org/pdf/training/natlbusagenda.pdf. በተሰኘ ድረ ገጽ ላይ በፈረንሳይኛና በዩክሬንኛ ይገኛል፡፡

ሴቶች በሚመሯቸው ቢዝነሶችና በንግድ ማኅበራት ተዘጋጅተው የተሳካ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ አድቮከሲ የተሠራባቸውን ምሳሌዎች በአባሪ «ሐ» ላይ ይመልከቱ፡፡

## መርጃ ቁጥር 14

## የተዋጣለት የሕግ ማማከር ፕሮግራምን እንዴት መቅረጽና መተግበር እንደሚቻል

በሀገራችሁ በርካታ ቁጥር ያላቸው በለውጥ የሚያምኑ ፖሊሲ አውጪዎች ኖረው ኢኮኖማያዊና ንግድ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የባለሙያዎች፣ የገንዘብ እና የንብረት እጥረት ሲኖርባቸው የሕግ አማካሪ ፕሮግራም ማካሄድ በጣም ጠቃሚ ነው የሚሆነው፡፡ የሕግ ማማከር ፕሮግራም ተግባር የተረቀቁ ሕጎችንና ደንቦችን በማጤን ያላቸውን ጉዳትና ጥቅም በቀላሉ ዳስሶ ማቅረብና ከዚያ በኋላ ለሕግ አውጪዎችና ለሕዝቡ ማከፋፈል ነው፡፡

*ከፖሊሲ አውጪዎችና አስተዳዳሪዎች ጋር በምትገናኙበት ጊዜ ጠቃሚ የሆኑ ነጥቦች!*

- *ግልጽ መሆን፣*
- *ተጨባጭነት ያለው ነጥብ ማቅረብ፣*
- *እውነተኛ መሆን፣*
- *ከዋና ነጥብ መጀመር(ከጥቃቅን ነጥብ አለመጀመር)፣*
- *ሰነዶችን አዘጋጅቶ መያዝ፣*
- *ረቂቅ አዋጁን ወይንም ሕጉን አስመልክቶ ዝግጁ መሆን፣*
- *የምታገኘውን ወይንም የምታገኛትን ባለሥልጣን የፖሊሲውን ረቂቅ አስመልክቶ የሚደረጉ ድምጽ አሰጣጦች ላይ እንዲሁም ፖሊሲው ወይንም አዋጁ በሚላክበት ወቅት ድግፍ እንዲሰጡ በግልጽ መጠየቅና*
- *ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌላቸውንና አጥጋቢ መልስ ልትሰጥባቸው የማትችልባቸውን ነጥቦች አለማንሳት::*

ይህን ማድረግ በፖሊሲ ላይ የሚደረገው ክርክር ግንዛቤ የተሞላው እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ የግሉ ዘርፍ የመንግሥትን ፖሊሲ የማውጣት ሂደት ቅርጽ በማስያዝ ጥሩ ምላሽ የሚሰጥበት እንዲሆን እድል ይሰጠዋል::

## የተሳካ የሕግ ማማከር ፕርግራም መሠረታዊ ገጽታዎች

የሚከተሉት ገጽታዎች የሕግ ማማከር ፕሮግራሙን ውጤታማነት የሚያዳብሩ ናቸው::

- <u>ተአማኒነት:-</u> እያንዳንዱ የሕግ ማማከር ፕሮግራም ወሳኝ ኢኮኖሚያዊ ትንታኔን መሠረት ያደረገ ሊሆን የሚገባው ሲሆን፣ የሰለጠኑ ባለሙያዎችና ሌሎች ወገኖች ጉዳዩን እንዲያጤኑትና ሂሳቸውንም እንዲሰነዝሩ ለማስቻል ስለጉዳዩ በበቂ ሁኔታ የሚዘረዝሩ ጽሑፎችም ተዘጋጅተው የሚቀርቡበት ነው::
- <u>በቀላሉ ማቅረብ:-</u> የሚዘጋጀው ማጠቃለያ በሀገሪቱ አጠቃላይ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ነገር ግን የአንዱን ወገን ፍላጐት ብቻ የሚጸረር (ለምሳሌ የቢዝነስ ወይንም የሠራተኛን) ሆኖ ጥርት ባለ ቀላል ቋንቋ መዘጋጀት አለበት::
- <u>የሚገኝ ማድረግ</u>:- የሚዘጋጀው ማጠቃለያ ታትሞ ለበርካታ ሰዎች መሠራጨት አለበት:: የሚቻል ከሆነ በመገናኛ ብዙሃን በኩል ማሠራጨቱ የበለጠ ሰፊ ቁጥር ያለው ሕዝብ ዘንድ ለማድረስ ይረዳል::

- <u>ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር የፖሊሲ ውይይት:-</u> በብዙ ሀገራት ቢሮክራቶች የማስተካከያ እርምጃዎች እንዳይወስዱ አዳጋች ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ:: የንግድ ድርጅቶች የመንግሥት ፖሊሲ ላይ ጫና ከመፍጠር አንጻር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የመንግሥት ኃላፊዎች እና ሕግ አውጪዎች ላይ ተጽእኖ ለማሳደር መሞከር አለባቸው::

(ምንጭ ዋላክ እ.ኤ.አ (1991) እና ሱላቫን እ.ኤ.አ (1999)- በwww.cipe.org.ላይም ይገኛል)

## ደረጃ ስድስት:የአድቮከሲ መሣሪያዎችን መምረጥ፣ ወቃታዊነት ያላቸውን ጉዳዮች መለየትና የጊዜ ሠሌዳ ማዘጋጀት

የአድቮከሲ ኮሚቴው የአድቮከሲ መርጃ መሣሪያዎችን ከመረመረ በኋላ ለእያንዳንዱ ወይንም ለጥቅል ጉዳዮች የትኛውን መርጃ ሠነድ መጠቀም እንዳለበት መወሰን አለበት:: ከዚያም አስቸኳይነት ያላቸውን ጉዳዮች ለይቶ በማውጣት ለእነርሱ ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል:: (የዚህን ዓይነት ተግባር መፈፀም ለማኅበሩ አባላት ጥቅም የሚያስገኝ ከመሆኑም በላይ ወደፊት ለሚሠሩ የአድቮከሲ ሥራዎችም ድጋፍ ለማሰባሰብ ይረዳል)::

- ጉዳዩ አስቸኳይ ከሆነ፣
- ጉዳዩን አስመልክቶ በወቅቱ በርካታ ድጋፍ የሚገኝ ከሆነ፣
- አድቮከሲው በመሠራቱ የማኅበሩ አባላት በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥቅም የሚያገኙ ከሆነ፣
- አፋጣኝ እርምጃ አለመወሰዱ በብርቱ የማኅበሩን አባላት የሚጐዳ ከሆነ፣
- አፋጣኝ እርምጃ አለመወሰዱ የፖሊሲ ለውጡን የወደፊት ለውጥ አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ:: (ይህ የሚሆነው የወቅቱ አስተዳደር የፖሊሲ ለውጡን የሚፈልገው ከሆነ ነው:: ነገር ግን ቀጥሎ የሚተካው አስተዳደር ምንአልባት ላይቀበለው ይችላል)

ኮሚቴው አስቸኳይ የሆኑትን ጉዳዮች በዚህ ዓይነት ከለየ በኋላ የትኛው ጉዳይ መቼ እንደሚከናወን የሚያሳይ አጠቃላይ የጊዜ ሠሌዳ ማዘጋጀት አለበት::

### የአጠቃላይ የጊዜ ሠሌዳ አወጣጥ ናሙና

| ጉዳዩ | የሚካሄድበት ጊዜ |
|---|---|
| የንግድ ፈቃድ ግዴታዎችን ማሻሻል | ከጥር-መጋቢት 2003 |
| የጡረታ ማሻሻያ | ከየካቲት- ሰኔ 2003 |

ከዚህ ቀጥሎ ኮሚቴው ለእያንዳንዱ ወይንም ለጥቅል ጉዳዮች የጊዜ ሠሌዳ ያወጣል:: በተወሰነ ጉዳይ ላይ የሚዘጋጀው የጊዜ ሠሌዳ በወጣው መርሀ ግብር መሠረት እያንዳንዱ ወይንም ጥቅል ጉዳዮች ግባቸውን የሚመቱበትን ጊዜ ማመላከት አለበት:: ኮሚቴው እያንዳንዱ እቅድ ግብ እንዲመታ በቂ ጊዜ ስለመስጠቱ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል:: ጉዳዩ

በፖሊሲ እና ሕግ አውጪዎች መቼ ውይይት እንደሚካሄድበትና ድምጽ እንደሚሰጥበት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባትም አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ግብ በእያንዳንዱ የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ ግልጽ በሆነና በሚሳካ መልኩ መቀመጥ አለበት። ይህም የኮሚቴው ሠራተኞች የጉዳዩን ሂደት ለመከታተል ያመቻቸዋል።

## ውስን የጊዜ ሠሌዳ አወጣጥ ናሙና

*ጉዳዩ፡- የንግድ ፈቃድ ግዴታዎችን ማሻሻል፣*

*አጠቃላይ የጊዜ ሠሌዳ ከጥር - መጋቢት 2003*

| ክንውን | ውስን የጊዜ ሠሌዳ |
|---|---|
| ከሌሎች የንግድ ማኅበራት ጋር መገናኘት | ጥር 15 |
| ቁልፍ ከሆኑ ፖሊሲና ሕግ አውጪዎች እንዲሁም ሕግ አስፈጻሚዎች ጋር መገናኘት | ጥር 15 |
| ቅድመ ማሻሻያ ቅንጅት መፍጠር | የካቲት 1 |
| ለፖሊሲ አውጪዎች፣ለንግድ ማኅበራትና በአጠቃላይ ለሕዝቡ የተለያዩ ዝግጅቶችንና ገለጻዎችን ማካሄድ እና የአድቮከሲ ሰነዶችን ማሠራጨት፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ ክንውን ማግስት ጋዜጣዊ መግለጫ ማሰራጨት | ከጥር 15- መጋቢት 1 |
| ከመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ጋር በመገናኘት የአድቮከሲ ሰነዶችን ማሠራጨት | ከጥር 15 - መጋቢት 1 |
| ቁልፍ ከሆኑ ፖሊሲ አውጪዎችና አግባብነት ከላቸው ድርጅቶች ጋር በመገናኘት የአድቮከሲ ሰነዶችን መስጠት | ከጥር 15 - መጋቢት 1 |
| የአድቮከሲ ሥልቱን መገምገም | የካቲት 15 |
| ከሕግ አውጪዎች ድምጽ አሰጣጥ ቢያንስ አንድ ሣምንት ቀደም ብሎ ቅንጅትን ማንቀሳቀስ | ከካቲት 1-30 (የድምፅ መስጫው ቀን ላይ በመመሥረት) |

የአድቮከሲ ኮሚቴው ሠራተኞች በየሠአቱ የአድቮከሲ ሥልቱን ውጤታማነት መገምገም አለባቸው። የጊዜ ሠሌዳው ግምገማው የሚካሄድበትን ቀንም ማመላከት አለበት። /ስልቱን በተገቢው ለመዳሰስ የሚረዳውን ዘዴ በደረጃ ስምንት ላይ ይመልከቱ/

## ደረጃ 7: የማኔጅመንት በጀትን መመደብ

በማኅበራችሁ የአድቮከሲ ስልት ላይ በመንተራስ የአድቮከሲ ኮሚቴው አባላት የአድቮከሲ ሥራ ጥረቱ የተሳካ እንዲሆን ያለውን ገንዘብና ሀብት በአግባቡ ይመድባሉ፡፡ ይህም በውስን ወይንም በጠቅላላው ነጥብ ላይ የሚሠራውን የአድቮከሲ ሥራ ከግቡ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑትን ሠራተኞች ለማሰባሰብና አስፈላጊውን ፋይናንስ ለመወሰን ይረዳል፡፡ በአጭር አገላለጽ፣ በእያንዳንዱ ጉዳይ ምን ያክል ሠራተኛ እንደሚያስፈልግ እና ለዚህም ምን ያህል በጀት እንደሚያስፈልግ የሚያመላክት ዝርዝር የሆነ በጀት መሥራት ጠቃሚ ነው፡፡

በጀቱ መሠራቱ ኮሚቴው የሚከተሉትን እንዲወስን ይረዳዋል

- ስልቱ በእውነታ ላይ የተመሠረተ መሆኑን፣
- ስልቱ መሻሻል የሚፈልግ መሆኑን፣
- መወገድ ወይንም መተላለፍ የሚፈልጉ ጉዳዮች ካሉ ለመመልከት፣
- መጨመር የሚገባቸው ነጥቦችን ለማካተት፣

---

*በመንግሥት ፖሊሲ ላይ የአድቮከሲ ሥራን ለመሥራት የሚነደፈውን ስልት የተዋጣለት ለማድረግ አስፈላጊ ነጥቦች*

- *በአጠቃላይ ንግድን የሚያውኩ ሕጐችንና ደንቦችን አስመልክቶ መረጃ ማሠራጨት፣*
- *ሕዝቡ ግንዛቤ እንዲኖረውና እውቀትን እንዲጨብጥ ሕግና ደንቦችን ተርጉሞና አብራርቶ ለሕዝቡ ማቅረብ፣*
- *በሚወሰዱ የሕግና ደንብ አካሄድና አቅጣጫዎች ላይ ተፅእኖ ማሳደር፣*
- *እየወጡ የሚገኙ ጉዳዮችን በመለየት ከሕግ መነሻ ሃሳቦች ቀድሞ መገኘት ወይንም የሚወሰዱ እርምጃዎችን ቅርጽ ማስያዝ፣*
- *የመንግሥት ባለሥልጣናት ስለ ጉዳዩ ሊረዱ የሚችሉበትን አመቺ መንገድ ማመቻቸት፣*
- *አባላት ሕግ አውጪዎችን አስመልክቶ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው መመሪያ መስጠት ፣*
- *የተወሰኑ የመንግሥት መሪዎችን ለመቀስቀስ ሕጋዊ ተሽከርካሪ መመደብ፣*
- *የሰዎችን እውቀት አካሄድ መዋቅርን ማደራጀት፣*

---

## ደረጃ 8: ግምገማ

በደረጃ ስድስት ላይ እንደተገለጸው የእያንዳንዱ የአድቮከሲ ስልት ውጤታማነት በየጊዜው መዳሰስ ይኖርበታል፡፡ ይህን ማድረግ የአድቮከሲ ሥራው በተያዘለት ጊዜ ውስጥ ዓላማና ግቡን መምታት አለመምታቱን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በመመለስ የአድቮከሲ ኮሚቴ አባላት የአድቮከሲ ስልታቸው ውጤታማ መሆን አለመሆኑን በትክክል ለመዳሰስ እና ብሎም መሠረታዊ ለውጦችን ለማድረግ ይችላሉ፡፡

- ጉዳዩ በእርግጥ ለማኅበራችን አባላት አስፈላጊ ነው?

- ጉዳዩ በማናቸውም መልክ ለውጥ አምጥቷል?
- ሌላ ዝርዝር ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል?
- ዓላማዎቹና ማከናወኛ ጊዜያቱ ተጨባጭ ናቸው?
- የአድቮከሲ ኮሚቴው የጊዜ ሠሌዳውን እያከበረ ነው?
- ዓላማውና የጊዜ ሠሌዳው ክለሳ ይፈልጋሉ?
- ትክክለኛውን የአድቮከሲ ዒላማ ለይተናል?
- የአድቮከሲ ግባችንን ከመምታት አኳያ እየተሳካልን ነው?
- ትክክለኛ የሆኑ ልዑካን አሉን?
- ልዑካኑ መልዕክታችንን ከማድረስ አኳያ ብቃት አላቸው?
- መልእክቱ መሻሻል ይፈልጋል ወይንስ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ነው?
- የአድቮከሲ ስልቶቻችን ውጤታማነት እያሳዩ ነው?
- በቂ የሰው ኃይልና ፋይናንስ ተሟልቷል?
- የተፈጠረው ቅንጅት ያሉትን አጋጣሚዎች በሚገባ ተጠቅሟል?
- ቅንጅቶቹ በተዋጣለት ሁኔታ እየተንቀሳቀሱ ናቸው?

በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ በመንተራስ የአድቮከሲ ኮሚቴው አስፈላጊ ለውጦችን ማድረግ አለበት፡፡ አንዳንድ ማሻሻያዎች ከመወሰዳቸው በፊት ግን የሚደረገው ለውጥ የስልቱን ሌሎች አካላት መንካት አለመንካቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ከግምገማው የተገኘውን ማንኛውንም መልካም ውጤት ለማኀበሩና ለቅንጅቱ አባላት በኢሜል፣ በፋክስ ወይንም በኒውስሌተር በመላክ የአድቮከሲ ሥራው በተቃና ሁኔታ እየሄደ እንደሚገኝ ለማሳየት ይችላል፡፡

# ክፍል አምስት: አባሪ ሰነዶች

## አባሪ . ሀ

**ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳን መቅረጽ**
**2003 - 2004 /እ.ኤ.አ/**

**የአሜሪካን ንግድ ምክር ቤት አንገብጋቢ ጉዳዮች ጥናት**

## 1. ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው ፖሊሲች

የአሜሪካን ንግድ ምክር ቤት ከዚህ ከሚከተሉት ውስጥ ለየትኛው ፖሊሲ ቅድሚያ ቢሰጥ እንደሚመርጡ ያመልክቱ

## ታክስ/የኢኮኖሚ ፖሊሲ

| | | እጅግ ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | በመጠኑ ከፍተኛ | ዝቅተኛ | አስተያየት የለኝም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የስቴትና የስጦታ ታክስን ማስወገድ | O | O | O | O | O | O |
| 2 | የጥቃቅን የንግድ ሥራዎችን የወጪ አበል ከፍ ማድረግ | O | O | O | O | O | O |
| 3 | የኤ ስ ኮርፖሬሽን ታክስ ደንብን ማሻሻል | O | O | O | O | O | O |
| 4 | የሕብረት ወይንም የግልን አማራጭ ዝቅተኛ ታክስ መቀነስ ወይንም ማስወገድ | O | O | O | O | O | O |
| 5 | የኀብረት ወይንም የግለሰብ ካፒታል ገቢ ታክስን መቀነስ ወይንም ማስወገድ | O | O | O | O | O | O |
| 6 | የሠራተኞችን ምደባ ደንብ ግልጽ ወይንም ቀላል ማድረግ(ሠራተኞች ከግል ተቋራጮች) | O | O | O | O | O | O |
| 7 | በአሁኑ ወቅት ያለውን የፌዴራል ታክስ ሥርዓት መቀየር ወይንም ማሻሻል | O | O | O | O | O | O |
| 8 | የጋራ የታክስ ኮሚቴው የሚቀርቡ የታክስ መነሻዎችን የሚገመግምበትን ሂደት ማሻሻል | O | O | O | O | O | O |
| 9 | ጥቃቅን ንግዶች ካፒታል እንዲያገኙ የሚያስችለውን የፌዴራል መንግሥት ፕሮግራም ማጠናከር | O | O | O | O | O | O |
| 10 | የመንግሥት ኮንትራት እድሎችን ማስፋፋት | O | O | O | O | O | O |

## የህግ ማሻሻያ

| | | እጅግ ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | በመጠኑ ከፍተኛ | ዝቅተኛ | አስተያየት የለኝም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ሕጋዊ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች ላይ መንግሥት የሚመሠርተውን ክስ ማስቆም(ምሳሌ የትምባሆና የጠመንጃ አምራቾች) | O | O | O | O | O | O |
| 12 | በቅጣት የተነሣ የሚደርሱ ከልክ ያለፉ ጥፋቶችን ማስቆም | O | O | O | O | O | O |
| 13 | የግጭት ማስወገጃ አማራጮችን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት መደገፍ | O | O | O | O | O | O |
| 14 | መንግሥትን ጨምሮ በሁሉም ፓርቲዎች ሙግት ላይ ተመሣሣይ ደንብ ተፈጻሚ መሆኑን ማረጋገጥ | O | O | O | O | O | O |
| 15 | «የተቀደሰ ኮንትራት»የሚባለውን መመሪያ በመከተል ስምምነቶችን ማጠናከር | O | O | O | O | O | O |
| 16 | የምርትና አገልግሎት ተጠያቂነትን በማሻሻል፣ ድርጅቶች በራሳቸው ምክንያት ላጠፉት ጥፋት ብቻ ተጠያቂ እንደሆኑ ማድረግ | O | O | O | O | O | O |
| 17 | በከሳሽ የሕግ ባለሙያዎች የሚመሠረቱ ክሶችን እና አመለካከቶችን ቁጥር ለመቀነስ «እላስ አክሽን»የተሰኘውን ሕግ ማሻሻል | O | O | O | O | O | O |
| 18 | ከአለቤስቶስ ጋር በተያያዘ በአሁኑ ሠዐት በድርጅቶች ላይ ተጠያቂነት እያመጣ ያለውን አሠራር ማሻሻል | O | O | O | O | O | O |
| 19 | የ«የሴኪዩሪቲ ክላስ አክሽን» ክስን አስመልክቶ ያለውን ሙግት ቁጥር ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ማገዝ | O | O | O | O | O | O |
| 20 | የአቃቢ ሕግን ክፍያ መወሰንን አስመልክቶ እንዲሻሻል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ | O | O | O | O | O | O |

ለቢሮ አገልግሎት
የሚውል
የደረሰኝ ቁጥር

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |

5442113123

## የክልል ማሻሻያና የአካባቢ ፖሊሲ

| | | እጅግ ከፍተኛ | ምጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | በመጠኑ ከፍተኛ | ዝቅተኛ | አስተያየት የለኝም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | ሕግ አውጪ ኤጀንሲዎች አዳዲስ ሕጎችን ለማጠናከር የሳይንስ ውጤቶችን መጠቀማቸውን ማረጋገጥ | O | O | O | O | O | O |
| 22 | ኤጀንሲዎች የሚያሰራጩት ኢንፎርሜሽን ትክክለኛና ተጨባጭ መሆኑ ማረገገጥ | O | O | O | O | O | O |
| 23 | የፌዴራል ኤጀንሲዎች በሥራ ላይ የሚገኘውን ሕግ በየወቅቱ በመከታተል መሻሻል የሚገባውን ማሻሻል መቀየር የሚገባውን መቀየራቸውን ማረጋገጥ | O | O | O | O | O | O |
| 24 | ሕግ አውጪ ኤጀንሲዎች በሚያወጧቸው ሕጐች አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች እየደረሰባቸው ያለውን ችግር መከታተሉን ማረጋገጥ | O | O | O | O | O | O |
| 25 | የአካባቢ ሕጐች ወጪን ያገናዘቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ | O | O | O | O | O | O |
| 26 | የአካባቢ ፖሊሲዎች ገበያ ቀመስ መሆናቸውን ማረጋገጥ | O | O | O | O | O | O |
| 27 | በአደጋ ላይ የሚገኙ ዝርያዎችን ለማቆየት የንብረት አስተዳደር ሥራው የሁሉንም ወገኖች ፍላጐት ያጣጣመ እንዲሆን አድርጎ ማሻሻል | O | O | O | O | O | O |
| 28 | በሳይንሳዊ ዘዴ የተዳቀሉ ውህዶችን ለሚይዙ ምግቦች የሚሰጠውን ደረጃ መቃወም | O | O | O | O | O | O |

## ዓለም አቀፍ ፖሊሲ

| | | እጅግ ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | በመጠኑ ከፍተኛ | ዝቅተኛ | አስተያየት የለኝም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 29 | ከዓለም የንግድ ድርጅት አባል ሀገራት ጋር በጋራ፣ አባል ካልሆኑት ሀገራት ጋር ደግሞ በተናጠል የውጭ ገበያን መክፈት | O | O | O | O | O | O |
| 30 | የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ፕሮግራሞች ገበያ መር እንዲሆኑ ማድረግ | O | O | O | O | O | O |
| 31 | የመንግሥት ድጐማ ተደርጐላቸው ወደ አሜሪካ ገበያ ከገቡ የውጭ ሀገር ምርቶች የአሜሪካንን ገበያ መታደግ | O | O | O | O | O | O |
| 32 | የውጪ መንግሥታት ወጪ ምርታቸውን እንዲደጉሙና ኢንቨስትመንታቸውን እንዲያስፋፉ የሚደረገውን ድጋፍና የሚሰጠውን እርዳታ በመቃወም አሜሪካን በውጭ ያላት የገበያ ድርሻ እንዲጨምር ማድረግ | O | O | O | O | O | O |
| 33 | በጓዶቻችንና በወደጆቻችን ላይ የአሜሪካን መንግሥት የሚጥለውን የኢኮኖሚ ማዕቀብ ማስወገድ | O | O | O | O | O | O |
| 34 | በውጭ ሀገር የሚኖሩ አሜሪካውያን የሚከፍሉትን ዳግም ታክስ ማስወገድ | O | O | O | O | O | O |
| 35 | የአሜሪካን የንግድ ስምምነት ብቃት የንግድ ስምምነት ባለሥልጣኑ በተቀላጠፈ ሁኔታ ለአሜሪካንፕሬዝዳንትእንዲያቀርብ በማስቻል ማጠናከር | O | O | O | O | O | O |
| 36 | የአዕምሮአዊ ፈጠራ ንብረቶችን የባለቤትነት መብትን አስመልክቶ የሚደረገውን ዓለም አቀፍ ጥበቃ ማጠናከር | O | O | O | O | O | O |
| 37 | የአሜሪካንን የነጻ ንግድ ቀጠና ንግድ ስምምነቶች ማሳደግ | O | O | O | O | O | O |
| 38 | በአሜሪካን ወጪ ምርቶች ላይ ከውጪ ምርት ታሪፍና ከታሪፍ ነጻ ከተሰኙ የታሪፍ ዓይነቶች ጋር በተያያዘ የሚታዩ ችግሮችን ማስወገድ | O | O | O | O | O | O |
| 39 | በሳይንስ ውጤቶች በመታገዝ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ለማውጣት የተጀመረውን ሥራ የፖለቲካ ቅርጽ ለማስያዝ የሚደረገውን ጥረት መከላከል | O | O | O | O | O | O |

ደረሰኝ ቁጥር

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |

5064113123

| # | ትራስንፖርትና መሠረተ ልማት | እጅግ ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | በመጠኑ ከፍተኛ | ዝቅተኛ | አስተያየት የለኝም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 40 | የትራንስፖርት ፕሮግራምን አስመልክቶ ያሉትን አማራጭ የገንዘብ ምንጮች መደገፍ (ምሳሌ የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ የጋራ መድረኮች) | O | O | O | O | O | O |
| 41 | የትራንስፖርት ፕሮጀክት አገልግሎቶችን የተቀላጠፉ ማድረግ | O | O | O | O | O | O |
| 42 | የአየር ማረፊያዎችን ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶችን ማገዝ | O | O | O | O | O | O |
| 43 | ብሔራዊ የውስጥ የትራንስፖርት መረባችንን ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት መደገፍ | O | O | O | O | O | O |

## 2. የአባሉ አስተያየት

ከእያንዳንዱ ጥያቄ ቀጥሎ ከቀረቡት ክቦች ውስጥ የእርስዎን አመለካከት የሚወክሉት ላይ ምልክት ያድርጉ:: መልስዎ ጉዳዩ ለእርስዎ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የራስዎን አስተያየት በትክክል የሚያሳይ ሊሆን ይገባዋል::

| # | የሠራተኞች ጥቅማ ጥቅሞች | በትክክል ነው | በአጠቃላይ ነው | በአጠቃላይ አይደለም | በፍጹም አይደለም | አስተያየት የለኝም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሠራተኞች በቤተሰብ ደረጃ ለሥራ አጦች የሚከፈለውን የማካካሻ ክፍያ መፈጸማቸውን መቃወም አስፈላጊ ነው? | O | O | O | O | O |
| 2 | የፌዴራል የዝቅተኛ ገቢ ጭማሪን መቃወም አስፈላጊ ነው? | O | O | O | O | O |
| 3 | አሠሪዎች ሠራተኞቻቸው የትርፍ ሠዐት ሥራ በሚሠሩበት ወቅት የማካካሻ ስልት ክፍያ እንዲፈጽሙ የፌዴራል የሠራተኞች አዋጅ መፍቀዱስ? | O | O | O | O | O |
| 4 | የቤተሰብ የሕክምና ፍቃድ ሕግ ስሞታን የመሳሰሉ ቴክኒካል የሆኑ ጉዳዮችን መዳሰሱ አስፈላጊ ነው? | O | O | O | O | O |
| 5 | ሠራተኛ ማኅበራት ለፖለቲካ ዓላማ ከሠራተኞችላይ በግዳጅ መዋጮን የመሰብሰብ ሥልጠናቸውን መገደብ ተገቢ ነው? | O | O | O | O | O |
| 6 | ከብሔራዊ ጥናት ጋር በተያያዘ ያለውን የሠራተኛ እጥረት ለመቅረፍ የስደተኞች ሕጉን መቀየር አስፈላጊ ነው? | O | O | O | O | O |
| 7 | የጡረታ ሕጉ የተወሳሰበ መሆን አሠሪዎች የሠራተኞቻቸውን የጡረታ ጊዜ በአግባቡ እንዲያመቻቹ የሚገድብ ነው? | O | O | O | O | O |
| 8 | ሠራተኞች የራሳቸውን የጤና ፕላን በማውጣት አሠሪዎች መዋጮን ለመወሰን የሚያስችላቸውን አሠሪዎችን ማዕከል ያደረገው የጤና ኢንሹራንስ አማራጭን መቅረጽ አስፈላጊ ነው? | O | O | O | | O |
| 9 | የጤና ፕላን ተጠያቂነትን አስመልክቶ የሚመጣ ማንኛውንም ማስፋፊያ መቃወም አስፈላጊ ነው? | O | O | O | O | O |

## ሌሎች የፌዴራል መንግሥት መመሪያዎች

| # | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የንግድ ድርጅቶች በፌዴራል መንግሥት ሥር ያሉ መሬቶችን ለማዕድን ልማት ፣ለከብት ግጦሽ፣ለነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ መጠቀም አለባቸው ? | O | O | O | O | O |
| 11 | ፌዴራል መንግሥት ለገበሬዎች የሚሰጠውን ድጎማ መቀጠል አለበት? | O | O | O | O | O |
| 12 | ሕግ አውጪ ተቋማት እንዲወጡ ባቀረቧቸውና አስፀድቀው እየተሠራባቸው ባሉ ሕጎች ላይ ካውንስሉ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት አለበት? | O | O | O | O | O |
| 13 | የማኅበራዊ ሴኪውሪቲ ሥርዓት ከ21ኛው ክፍለ ዘመን ጋር በተጣጣመ መልኩ መሻሻል አለበት? | O | O | O | O | O |
| 14 | የፌዴራል መንግሥት ኢንተርኔት ላይ ሕግ ወይንም ክልከላ ማውጣት አለበት? | O | O | O | O | O |
| 15 | የገበያ መረጃ በኢንተርኔት የሚያገኙትና የማያገኙ የችርቻሮ ድርጅቶች በአንድ ደረጃ መታየት አለባቸው? | O | O | O | O | O |
| 16 | የመንግሥት የምግብ ደህንነት አሠራር በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ብቻ መሠራት አለበት? | O | O | O | O | O |
| 17 | ሰዎች ለራሳቸው ምግብና የምግብ ንጥረ ነገር ምርጫ እራሳቸው ኃላፊነት መውሰድ አለባቸው ወይንስ ሌላ የመንግሥት ሕግ መውጣት አለበት? | O | O | O | O | O |

ደረሰኝ ቁጥር

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |

3532113121

**1** የሥራ ዘርፍ (እባክዎን አንድ ብቻ ምልክትያድርጉ)

- ○ ኮሙዩኒኬሽን
- ○ ኮንስትራክሽን
- ○ አከፋፋይ
- ○ ኤሌክትሪክ/ጋዝ
- ○ ፋይናንስ/ኢንሹራንስ/ሪልኤስቴት
- ○ ምግብና/የእርሻ ንግድ
- ○ ጤና አጠባበቅ
- ○ ኢንፎርሜሽን/ቴክኖሎጂ
- ○ ኢንተርኔት/ኢ-ኮመርስ
- ○ አምራች
- ○ ማዕድን
- ○ ችርቻሮ
- ○ አገልግሎት
- ○ የንግድ ማኅበር
- ○ ትራንስፖርት
- ○ ሌላ

**2.** የሠራተኞች ብዛት:- ○ ከአሥር በታች ○ ከአሥር እስከ 49 ○ ከ50-99 ○ 100-249 ○ ከ250-499 ○ ከ500-499 ○ 5ሺ. እና ከዚያ በላይ

**3.** በብሔራዊ አገልግሎት ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ብዛት ☐ ☐☐☐

**4.** ከንግዳችሁ ውስጥ በሽርክና የተያዘው በመቶኛ ○ የለም ○ ከ10-25 በመቶ ○ ከ26-50 በመቶ ○ ከ51-75 በመቶ ○ ከ76-100

5. ድርጅታችሁ በዓለም አቀፍ ንግድ ተሰማርቷል ○ አዎ ○ አይደለም

5ሀ. የተሠማራ ከሆነ በየትኛው ዘርፍ እንደሆነ ያመልክቱ

○ አስመጪ ○ ላኪ ○ የውጭ ሀገር ሥራ ○ ዓለም አቀፍ የሽርክና ንግድ ○ የውጭ ድርጅቶች ውክልና

6. ድርጅታችሁ በመንግሥት ሥራ ውስጥ ተሳታፊ ነው? ○ አዎ ○ አይደለም

# የምላሽ መልዕክት

የመጀመሪያ ደረጃ መልዕክት የፈቃድ ቁጥር 10004 ዋሽንግተን ዲሲ

## ክፍያው የሚሸፈነው በተቀባዩ ነው

የአሜሪካ ንግድ ምክር ቤት
የንግድ መረጃና ልማት
1615 ዘጐዳና ኤን ደብሊው
ዋሽንግተን ዲሲ 20077-2565

ስም

የአባት ስም

የድርጅቱ ስም

ኢሜል

የአሜሪካን ንግድ ምክር ቤት የአባልነት ቁጥር

ፋክስ ☐☐☐ - ☐☐ - ☐☐☐

<u>ማስታወሻ</u>

የአባልነት ቁጥራችሁ በንግድ ምክር ቤቱ የመላላክ ግንኙነት ዝርዝር ላይ ከስማችሁ በላይ ታትሟል።

## የአሜሪካን ንግድ ምክር ቤትን በመርዳትዎ እናመሰግናለን

## እባክዎን ሞልተው ካጠናቀቁ በኋላ እስከ መስከረም 22 ቀን 2000 ይላኩልን

ሲልኩ በቀላሉ ሦስት ቦታ አጥፈው በፕላስተር በማያያዝ ይላኩት።

የሚላከው በዩ ኤስ ሜይል በኩል ነው -ፖስታ አያስፈልገውም **36411131**

# አባሪ ለ፡ በምሥራቅ አውሮፓ ማሻሻያዎችን ለማበራታት ስለተፈጠሩ ቅንጅቶች

## ሮማንያ

ስልታዊ ቅንጅቶች የሚወሰዱ ማሻሻያዎችን ከማበረታታት አንጻር ለሚሠራ የአድቮከሲ ሥራ ቁልፍ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ በሽግግር ላይ በሚገኙ እና የዘርፍ ማህበራት ተሸንሽነው በተከፋፈሉባቸው ሀገራት ማኅበራት በዚህ ቅንጅትን በመፍጠሩ ዘዴ ላይ ከፍተኛ ፍላጐት አሳይተዋል፡፡

በሮማንያ የዘርፍ ማኅበራትና የንግድ ድርጅቶች በከፍተኛ ሁኔታ የተከፍፈሉ ናቸው፡፡ ይህ በመሆኑም የሥራ ፈጣሪነት ዓለም አቀፍ የጥናት ማዕከል (ICES) የንግድ ማኅበራቱ ሥልታዊ ኅብረት የፈጠሩበትን (ICES) የተሰኘ ኅብረት የሚፈጠርበትን ልዩ ፕሮግራም አዘጋጅቷል፡፡ የጥናት ማዕከሉ ቡድን ባለሙያዎች ጥናቱን በሚያካሂዱበት ወቅት አብዛኛዎቹ ዋና ዋና የንግድ ማኅበራት በሽግግሩ የመጀመሪያ ጊዜያት የመንግሥት የሆኑ ድርጅቶች ወይንም በቀድሞው የኮሚኒስት አሰያየም ማነቆ ሥር ወድቀው የነበሩ ማኅበራት እንደሆኑ ለማወቅ ችለዋል፡፡

የጥናት ማዕከሉ ቡድን አባላት በመቀጠልም ከግለሰብ ሥራ ፈጣሪዎች (ኢንተርፕረነሮች) ጋር አብሮ መሥራቱን በመቀጠል በሮማንያ አንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ሶፍትዌርን በመሳሰሉ ንግዶች ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎችችና የአነስተኛ ንግዶች ማኅበራት በሀገሪቱ የገበያ ኢኮኖሚ እንዲሰፍን ግፊት ሲያደርጉ እንደነበር ለማወቅ ችለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ማኅበራቱ በተናጠል ደካማ የነበሩ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው በግላቸው ስላላቸው አስተዋጽኦም ግንዛቤ አልነበራቸውም ነበር፡፡ በማኔጅመንት ዙሪያ ሥልጠና በሚካሄድበት ጊዜ ከሚመስሏቸውና የጋራ ዓላማ ካላቸው ማኅበራት ጋር መቀራረብና ቡድን መሥራት ጀመሩ፡፡ ከዚያም ተነስተው ዛሬ የንግድ ማኅበራቱ ስልታዊ ኅብረት አባላት፣ ጥልቀት ያለው የሕግ አማካሪ ፕሮግራም በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡

## ፖላንድ

የፖላንድን ከአውሮፓ ኅብረት ጋር መጣመር አስመልክቶ ለመንግሥት የፖሊሲ አማራጮችን ለማቅረብ በፖላንድ የንግድ ድርጅቶች ኅብረት መሥርተው ነበረ፡፡ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1998 ደግሞ የንግዱ ኅብረተሰብ ተወካዮች፣ የንግድ ድርጅቶች ኅብረትና የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት በመሆን የታክስ ማሻሻያ መንገዶችን የሚያጠና አንድ ኮሚቴ አቋቁመው ነበር፡፡ ኮሚቴው አጠቃላይ የታክስ ተመንን እና የታክስ ክፍያን ሂደቶች

ቀላል ማድረግ ላይ ጥናት በማካሄድ የጥናቱን ግኝቶች ካጠቃለለ በኋላ ለፓርላማው አቅርቧል:: ይሁን እንጂ በነጥቡ ላይ በፓርላማው ውይይት ከተካሄደ በኋላ ፓርላማው የታክስ ማሻሻያ ጉዳይን አስመልክቶ ውሳኔ መስጠትን ለሌላ ጊዜ አስተላልፎታል::

እዚህ ደረጃ ላይ ቢደረስም የግል ንግድ ድርጅቶችና ዲሞክራሲ ማዕከል የተሰኘ ተቋም ፕሬዚዳንትና የዚያው ኮሚቴ አባል የሆኑት ሚዚስለው ባክ ፓርላማው የታክስ ማሻሻያውን አስመልክቶ ውሳኔ ያስተላልፋል የሚል ተስፋ ነበራቸው:: ይኼንንም ሲገልፁት «በፓርላማው ውስጥ በአሁኑ ወቅት በጥንካሬያቸው የሚታወቁት የሠራተኛ ማኅበራት እኛ የምናቀርባቸውን ብዙዎቹን ሃሳቦች የሚቃረኑ ናቸው:: በመሆኑም ከሁሊም አስቀድመን እነርሱን ማሳመን አለብን» ብለዋል::

እኚሁ ሰው ይሄው ኮሚቴ ፖላንድ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር እንድትተሳሰር የሚያደርጋትን ወሳኝ የኢኮኖሚ ማሻሻያን አስመልክቶ አቋሙን ለመንግሥት የማቅረቡን ሂደት መቀጠል አለበት ባይ ናቸው:: በመቀጠልም «ቢዝነሳችን ከኅብረቱ ከመጣመር ጋር ተያይዘው ለሚመጡ ውድድሮች ብቁ እንዲሆን ከተፈለገ በተለይ ከታክስ ጋር የተያያዙ በርካታ ሕጐችን ማሻሻል ያስፈልጋል:: መንግሥት ይኸንን አስመልክቶ የማሻሻያ ለውጦችን ለማምጣት ከአራት እስከ አምስት ዓመት አለው:: ደግሞም የንግዱን ኅብረተሰብ ማዳመጥ እንደሚገባው ያውቃል» ብለዋል::

እንደ ባክ አገላለጽ ከሆነ ከዚህ ተሞክሮ ለመማር የሚያስፈልገው ዋና ነጥብ የንግዱ ኅብረተሰብ የጋራ አቋም ምን ጊዜም ውጤታማ መሆኑን ነው::«አቋምና ውሳኔን ለመንግሥት ከማሳወቅ አንጻር የግሉ ዘርፍ ድርጅቶች ኅብረት ውጤታማ ነው» ይላሉ እኚሁ ባክ:: በማከልም«ቀድሞ ነጋዴው ይናገር የነበረው ድምጻቸውን በተገቢ ሁኔታ በማያስሙት በተለያዩ የንግድ ድርጅቶች አማካኝነት ነበር:: በያዝነው ዓመታት ግን የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የተደራጅቶ ግንባር በመፍጠሩና መንግሥት ላይ በአግባቡ ቅስቀሳ በማካሄዱ እውቅና ሊያገኝ ችሏል፡፡ በዚሁ ዓይነት የጋራ ፍላጐት ያላቸው ቢዝነሶች ቅንጅት ከፍተኛ የቅስቀሳ ኃይል ሊሆን ይችላል» ብለዋል::

## አባሪ ሐ፡ በዓለም ዙሪያ የተዋጣላቸው ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳዎች

### ሀይቲ

በሀይቲ ውስጥ የነበረውን የፖለቲካ ኪሣራ ለማስተካከል እርምጃ እየተወሰደ በነበረበት ወቅት በመንግሥት ፖሊሲ ዙሪያ የንግዱ ኅብረተሰብ ጠንካራ ድምጽ እንዲኖረው እንደሚፈልጉ በርካታ የግሉ ዘርፍ መሪዎች ለሳይፕ ገልፀው ነበር:: በዚህም ላይ በመንተራስ በዚያን ወቅት ሳይፕ ከሲ ኤል አይ ኤስ እና ከሌሎች አሥር የንግድ ማኅበራት ጋር በመሆን ብሔራዊ የብዝነስ አጀንዳን ቀርጿል፡፡ የቢዝነስ አጀንዳው በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በተላለፉ የማሻሻያ ቅድሚያዎችና በተወሰኑ የፖሊሲ ማሻሻያ አስተያየቶች ላይ ያተኮረ ነበር:: ይህም አጀንዳ ለሀገሪቱ ፕሬዚዳንትና ወሳኝ ፖሊሲ አውጪዎች ባለፈው የአውሮፓውያኑ 2002 ቀርቧል:: የፖለቲካው አጣብቂኝ

እንደቀጠለ ቢሆንም በዚያን ጊዜ የሰፊው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አባላት ተስፋ አነስተኛ ንግዶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ማሻሻያ ሲፈፀም ማየት ነበር፡፡

ከዚህም በመነሣት የአትኩሮት ቡድኖች በመባል የሚታወቁት በጉዳዩ ላይ አግባብነት ያላቸውና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቡድኖች ውይይት፣ በንግድ ዘርፎች ስምንት፣ በክልል ደረጃ ደግሞ አራት ውይይቶች ተካሄደዋል፡፡ በዚህ መድረክ በንግዱ ላይ በተፈጠረ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ችግሮች ላይ በአጠቃላይ፣ በተናጠል ደግሞ ከዚህ በሚከተሉት ዘርፎች ተመሣሣይ አቋም ያላቸውን የንግድ ማኅበራት መሪዎችን ለማሰባሰብ ተችሎአል፡፡ በተናጠል ንግድ ነክ ችግር ያለባቸው የላኪ ኢንዱስትሪዎች ስብስብ፣ ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ እርሻና የእርሻ ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ችርቻሮ፣ የባንክና ኢንሹራንስ ዘርፎች ናቸው፡፡ እነዚህም ዘርፎች በኋላ አንገብጋቢ ለሆኑት ችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ በጋራ ጠቁመዋል፡፡

በመጨረሻም የዚህ ፕሮጀክት ተሣታፊዎች በሀይቲ ንግድን አስመልክቶ ያሉትን ችግሮች ግልጽ በሆነ መልኩ የሚያመላክት ረቂቅ የቢዝነስ አጀንዳ አዘጋጅተዋል፡፡ ችግሮቹን ከመለየቱ በተጨማሪም መንግሥት በቅርብ ጊዜ ውስጥ ችግሮቹን ለማስወገድ ሊወስዳቸው ስለሚገባው ጠቃሚ፣ ወሳኝና መሠረታዊ እርምጃዎች ቀላል በሆነ መንገድ አቅርበዋል፡፡

ዛሬ ፕሮጀክቱ ከፍተኛ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን ሽፋንን ተጐናጽፏል፡፡ ይህም በመሆኑ የቢዝነስ አጀንዳውን የሚመለከቱ ሁለት መጣጥፎች በሁለት ስመጥሩ ጋዜጦች ላይ ታትመው ወጥተዋል፡፡ ሕትመቱ ፕሮጀክቱን አስመልክቶ ድጋፍ ማሰባሰብ ላይ በሕዝቡ መካከል ግንዛቤ በመፍጠር ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ እነዚህ መጣጥፎች ያተኮሩት በፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች አማካኝነት የሀይቲ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን በማበረታታት ዙሪያ ወሳኝ የሆነ ተሣትፎ እያደረገ እንደሚገኝ በማሳየት ላይ ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን፣ መጣጥፎቹ ይኸው የግል ዘርፍ በራሱ በግል ዘርፉ መካከል እንደዚሁም በግል ዘርፉና በመንግሥት መካከል ጠቃሚ የሆነ የውይይት መድረኮችን እያካሄደ እንደሚገኝና ይህም እንቅስቃሴ በሀገሪቱ አመቺ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር፣ በዚሁም አማካኝነት የሥራ መስክ ብሎም የኢኮኖሚ እድገት እንደሚፈጠር አትቷል፡፡

## ማላዊ

የማላዊ ነጋዴ ሴቶች ብሔራዊ ማህበር (NABW) በማላዊ ያለትርፍ የሚንቀሳቀስና ሴቶች ለሚመሯቸው አነስተኛ ንግዶች ድጋፍ የሚሰጥና በማላዊ መንግሥት ውስጥም የማኅበሩን አባላት ጥቅም የሚያስጠብቅ ነው፡፡ ይህ ማኅበር «ለእርምጃ ብሄራዊ ጥሪ» በተሰኘ ፕሮግራሙ ነጋዴ ሴቶች ንግድ ለማቋቋም እና ለማሳደግ በተለይ በአራት የንግድ ዘርፎች ያሉባቸውን ችግሮች ለይተው እንዲያስቀምጡ አድርጓል፡፡ ዘርፎቹም የእርሻ ንግድ፣ ሶፍት ጉድስ (ጨርቃ ጨርቅ፣ አልባሳትና እደ ጥበብ) ፣ ቱሪዝም እና ሙያዊ አገልግሎቶች (ሕግ፣ሒሳብ እና

ማማከር) ናቸው። «የእርምጃ ብሔራዊ ጥሪው» የተጀመረው እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1998 ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በተገኙበት ነው። በዚያ ስብሰባ ላይ የነጋዴ ሴቶች ማኅበር አባላት በእንቅስቃሴው ተለይተው የወጡት የአራቱ ዘርፎች ችግሮች እንዲቀረፉ ለመንግሥት ባለሥልጣናት ጥሪ አስተላልፈዋል።

ከዚህም በተጨማሪ በማላዊ ያለው ሴቶች የመሬት ባለቤት እንዳይሆኑ አድልኦ የሚፈጥረው የመሬት ባለቤትነት ሥርዓት ነጋዴ ሴቶች መሬትን በማስያዝ ገንዘብ እንዳይበደሩ የሚከላከል በመሆኑ እንዲሻሻል ጠይቀዋል። በዚሁ የማላዊ ነጋዴ ሴቶች ብሔራዊ ማኅበር ጥረት ፍሬ ማፍራት ጀመረ። ከዚህም በመነሣት ማኅበሩ የመሬት ክፍፍሉን መለወጥንና በሴቶች የሚመሩ ንግዶች ላይ የመንግሥት አገልግሎትን ማሻሻልን አስመልክቶ ለመንግሥት ቋሚ ኮሚቴዎች ጠቃሚ ግብአቶችን ሰጥቷል። ከዚህም በተጨማሪ መንግሥት አማራጭ የግዢ እቅድን በማዘጋጀት የመንግሥት ግዢዎች ሴቶች ከሚመሯቸው ንግዶች ላይ እንዲፈፀም የተስማማ ሲሆን፣ ይህ በመደረጉም ወደ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት የሚገቡ ሴቶችን ቁጥርም ለመጨመር ተችሏል። ለበለጠ መረጃ www.cipe.org በተሰኘው ድረ ገጽ የወቅቱ የምጣኔ ሀብት ለውጥ የተሰኘውን መጣጥፍ ይመልከቱ።

## ናይጄሪያ

እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ1998 የናይጄሪያ የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና እርሻ ማኅበራት ንግድ ምክር ቤት ጠቃሚ በሆኑ ንግዶችና ኢኮኖሚ ነክ ጉዳዮች ላይ አቋሙን የሚገልጽ ሰነድ በብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳነት አቅርቧል። ይህ 33 ገጽ ያለው ሰነድ የናይጄሪያን የኢኮኖሚ አመራር ብቁና የተዋጣለት ለማድረግ የሚያስችሉ 30 ዋና ዋና ጉዳዮችን የዳሰሰ ነው።

በዚህ ሰነድ ውስጥ የታክስ ማሻሻያ፣ የውጪ ንግድ፣ ፕራይቬታይዜሽን ፣ የውጪ ብድር፣ ከነዳጅ ወጪ የሆኑ ወጪ ምርቶች፣ የገጠር ልማት፣ የፖለቲካ መረጋጋትና የናይጄሪያ ስቶክ ኤክስቼንጅ ማሻሻያ ተካተዋል። ይህም ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳው የመንግሥት ፖሊሲዎችን አስመልክቶ ተጽእኖ የማሳደሩ ስልት አካል ነበር። እንደ ናይጄሪያ የኢንዱስትሪ፣ የማዕድንና የእርሻ ማኅበራት ንግድ ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር ለውረንስ አዲኩንሲ ከሆነ የማኅበራቱ ንግድ ምክር ቤት በብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳው በመታገዝ ያከናወነው ተግባር የናይጀሪያ መንግሥት ወድድርን የሚያውኩ በርካታ ሕጐችን እንዲያስወግድ አበረታተውታል። በተለይ ቀድሞ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ወድቆ የነበረው የቴሌኮሙኒኬሽን ኢንዱስትሪ ውድድር ክፍት ለመሆን በቅቷል። ነዳጅ ዘይትን የማጣራት ሥራ ዘርፍም በአሁኑ ወቅት ለግሉ ዘርፍ ክፍት እየሆነ በመምጣቱ ድርጅቶች ነዳጅን ከውጪ በማስመጣት መሸጥ ጀምረዋል። ከሁሉም በላይ የናይጄሪያ መንግሥት በአሁኑ ወቅት የግሉ ዘርፍ የሚሰነዝራቸውን አመለካከቶች ለመቀበል ይበልጥ ፈቃደኝነትን እያሳየ የመጣ መስሏል። ለተጨማሪ መረጃ

በቀጥታ መገናኛ መስመር (On line) http.//www.cipe.org. ላይ የሚገኘውን Economic Reform To day መጣጥፍ ይመልከቱ::

## ፓራጓይ

ወደ 70 የሚጠጉ በፓራጓይ በኢንዱስትሪ፣ በአምራች እና በኮሜርሻል ዘርፎች የተሰማሩ ድርጅቶችን በመወከል የንግዱን ኅብረተሰብ መሠረታዊ ድምጽ ለመንግሥት የሚያሰማው የናይጄሪያ አምራቾች፣ የኢንዱስትሪና የኮመርስ ፌዴሬሽን (FEPERINCO) ነው:: ፌዴሬሽኑ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ኅብረት ፈጥሮ የማሻሻያ አድቮከሲ በመሥራት የሕግ አማካሪ ፕሮግራምን ለመጀመር ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳን ቀርጿል:: አጀንዳው የገበያ ማሻሻልን አስመልክቶ የተወሰነ የፖሊሲ አቋምን ለመያዝ የሚያስችሉ አጠቃላይ የኢኮኖሚ መርሆችን የያዘ ነው:: ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳው የመንግሥትን የኢኮኖሚ መርሀ ግብር በመቃኘት የሀገሪቱን የዲሞክራሲና የገበያ ኢኮኖሚ ሽግግር የሚያጠናክሩ ሌሎች ማሻሻያዎችን ለይቶ አውጥቷል:: አጀንዳው እንደ የመንግሥት አስተዳደርን፣ ፖሊሲ የማውጣት ሂደት ግልጽነትን፣ የምርጫ ማሻሻያን፣ የሰው ኃይል ለካፒታል መዋዕለ ነዋይን፣ መደበኛ ያልሆኑ ቢዝነሶችን፣ አዲስ የሕግ ማዕቀፍን እና ድህነት ቅነሳን የመሳሰሉ የማሻሻያ እድሎች የሚታይባቸውን ነጥቦችም ለይቶ አውጥቷል::

ይህ አጀንዳ የግሉን ዘርፍ አንድ ወጥ ድምጽ ለመንግሥት ያቀረበ በመሆኑ የተሣካለት ነበር:: ሁሉንም ማለትም የመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎችንና ራሱን የንግዱን ኅብረተሰብ ስለ ፖሊሲ ማሻሻያ ከማሳወቅ አንጻር በከፍተኛ ሁኔታ መመሪያ ሰጪም የነበረ ሲሆን፣ ሁለቱንም በመልካም አስተዳደሩ ግንባታ ሂደት ውስጥ ተሣታፊ እንዲሆኑ በማስገደድ ለዲሞክራሲ ያላቸውን ቁርጠኝነት አጠናክሯል::

## ዩክሬን

በዩክሬን ውስጥ ሳይፐ የተወዳዳሪ ማኅበረሰብ ተቋም እና የዩክሬናውያን ነጻ ፖለቲካዊ ምርምር ማዕከል ከተሰኙ ሁለት ድርጅቶች ጋር በመሥራት ላይ ነው:: ከድርጅቶቹ ጋር የሚሠራው በብሔራዊ ደረጃ የንግድ ተወካዮችን በማሳተፍ ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ለመቅረጽና ይኼንንም ለብሔራዊ ፖሊሲ አውጪዎች ለማቅረብ ነው::

የዩክሬናውያን ብሔራዊ የቢዝነስ አጀንዳ ቅድሚያ የሚሰጣቸውና አንገብጋቢ የሆኑትን ሕግና ደንቦች በማውጣትና እነርሱንም ይዞ ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር በማገናኘት የዩክሬን የንግድ ኅብረተሰብ ከመንግሥት ፖሊሲ ጋር በተያያዘ ያለበትን ችግር ለመቅረፍ ቁልፍ መሣሪያ ሆኗል:: ዛሬ የንግድ ማኅበራት ተወካዮች፣ ሥራ ፈጣሪዎች እና የመንግሥት ባለሥልጣናት የሚገኙበት አንድ የሚመለከታቸው ወገኖች ስብሰባ ተካሂዶ፣ በኪኢቭ የሚገኙ ኪወስኮች

እንዳያድጉና እንዳይበለጽጉ የሚያደርጉ ማነቆዎችን ለይቶ ካወጣ በኋላ መሰናክሎቹን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችንም አብሮ ነድፏል።

## አባሪ መ: ዓለም አቀፍ የሕግ አማካሪ ፕሮግራሞች

የዶሚኒካ ሪፓብሊክ የሕግ አማካሪ አገልግሎት በመላው ዓለም ለታዩ ተመሳሳይ የሕግ አማካሪ አገልግሎቶች እንደናሙና ያገለገለ ተመራጭ ተሞክሮ ነበር። በደቡባዊው ንፍቀ ክበብ በሚገኙት በአርጀንቲና ፣ ብራዚል፣ ማዕከላዊ አሜሪካ፣ ቺሊ፣ ኢኳዶር፣ ኤልሳልቫዶር፣ ጓቲማላ፣ ፓራጓይ፣ ፔሩና ኡራጓይ የዚህኑ ፈለግ የተከተሉ እንቅስቃሴዎች በመካሄድ ላይ ናቸው። በምስራቅ አውሮፓም በቀድሞዋ ቼኮዝላቫኪያ ፣ ሀንጋሪና ፖላንድ የሚገኙ ድርጅቶች የሕግ አማካሪ አገልግሎትን በማደራጀት ላይ ናቸው። በሴሪላንካ የሚገኝ አንድ ድርጅትም የዚህን ዓይነት ፕሮጀክት በመጀመር በኢስያ የመጀመሪያው ሆኗል። በእርግጥ በእያንዳንዱ ሀገር የተደረገው እንቅስቃሴ በእያንዳንዱ ሀገር የሕግ አሠራር ላይ የተመሠረተ ነው። ይሁን እንጂ ፖለቲከኞችን የመቀስቀስና መረጃ የመስጠቱ መሠረታዊ አካሄድ ተመሳሳይ ነው።

### የዶሚኒክ ሪፓብሊክ

በበርካታ ሀገሮች እንደሚያጋጥመው ሁሉ የዶሚኒካ ሪፓብሊክ ሕግ አውጪዎች ሕግን በመተንተን ሥራ ላይ ያላቸው የሰው ኃይል ውስን ነበር። እነዚህ አካላት የራሳቸው የሆነ ሠራተኛ ያልነበራቸው ሲሆን፣ በጣም ውሱን የሆኑ የኮሚቴ ሠራተኞች ብቻ ነበሩ የነበሯቸው። በዚህም የተነሣ ሕግ አውጪው ሕጉ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ መተንተንን በሚመልከት በመንግሥት ቢሮክራቶች ተጽእኖ ሥር የወደቀ ነበር።

ይህ በመሆኑም ነበር በዶሚኒካ ሪፖብሊክ ሲ.ኢ.ኦ የተሰኘው በኢኮኖሚ ግንዛቤ ማስጨበጥ ዙሪያ የሚሠራው ማዕከል እ.ኤ.አ በ1986 በሳይፐ በመታገዝ ሕግ የማማከር ፕሮግራሙን የጀመረው። ማዕከሉ በአጭር ሪፖርቱ በጉባኤው አሳሳቢነት ኢኮኖሚያዊ ሕጐች ላይ ትንታኔን በመስራት ሕጉ በመንግሥትና በግል ዘርፍ፣ በብሔራዊው በጀት እና በሕግ ሥርዓቱ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ አሳጥሮ አቅርቧል። ሪፖርቱ የተጠቃለለው ሕጉን አስመልክቶ መጽደቅ፣ መሻሻል፣ መሠረዝና መጨመር ያለባቸውን ማሳሳቢያዎች በዝርዝር በማስቀመጥም ጭምር ነው።

ሪፖርቱ የጉባኤውን ፕሮግራም በመንተራስ ለሕግ አውጪዎች እና ለመላው ሕዝብ ተሰራጭቷል። ተቋሙ በዚህ ሪፖርት አማካኝነተ የተወሰኑ ኢኮኖሚያዊ ሕጐችና ደንቦች የሚያስከትሉትን ችግር ለሕግ አውጪዎች፣ ለመገናኛ ብዙሃን እና ለሕዝብ ያመለከተ ሲሆን፣

ለመገናኛ ብዙሃን እና ለተወሰኑ ከመንግሥት ጋር ግንኙነት ላላቸው ወገኖች ደግሞ በተለይ ሕግ አጪዎችን ተጠያቂ ሊያደርጉ የሚችሉበትን መረጃዎች ሰጥቷቸዋል፡፡

## አርጀንቲና

በአርጀንቲና ይኸው የህግ ማማከር ተግባር የተከናወነው አይ.ኢ.ኢ.አር፣ኤ.ኤል በተሰኘ በአርጀንቲና ነጋዴዎች የሜዲትራንያን ፋውንዴሽን በመታገዝ በአርጀንቲና እና ላቲን አሜሪካ የኢኮኖሚ ምርምሮችን በሚያካሂድ ማዕከል ነው፡፡ የአርጀንቲናውን ፕሮጀክት ለየት የሚያደርገው ሪፖርቱ በብሔራዊውና በክልል ደረጃ መዘጋጀቱ ነው፡፡ ይህ የተደረገውም የክልል የሕግ መወሰኛ ጉባኤዎች ራስ ገዝ በመሆናቸው ነው፡፡

የሕግ ኤክስፐርቶች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሦስት ሪፖርቶችን አዘጋጅተው «ኖቪዳድስ ኢኮኖሚካስ» በተሰኘው የማዕከሉ መጽሔት ላይ በማተም ለብሔራዊና ለክልል ሕግ አውጪዎች ፣ ለመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ለንግድና ሙያዊ ማኅበራት እንዲሁም ለመገናኛ ብዙሃን አሠራጭተዋል፡፡ የተሠራው የሕግ ትንታኔ ሪፖርት የግሉን ዘርፍ ፍላጐት የሚያንፀባርቅ መሆኑን ከማረጋገጥ አንጻር ማዕከሉ ወርሃዊ ስብሰባ በመጥራት የግሉ ዘርፍ አባላት አስተያየቶቻቸውን እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የዚሁ ማዕከል ባልደረቦች ከፖለቲካ ገለልተኝነት በፀዳ መልኩ ሁሉንም ሕግ አውጪዎች ያማክራሉ፡፡

ሕግ አውጪዎች ሪፖርቱን «ብቃት ለሌለው ፓርላማ ብቃት ያለው ዘዴ» ሲሉ ይጠሩታል፡፡ ምክንያቱም ሰነዱ ስልታዊ ሆኖ የሕግ አውጪው ክርክር በጣም ጠቃሚ በሆነ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩርና ሕግ አውጪዎች በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲሰጡ በቀላሉ መረጃን የሚያስጨብጥ ሆኖ በመቅረቡ ነው፡፡ ጋዜጠኞችም ሪፖርቱ ሕግ የማውጣት ሂደት ላይ አስፈላጊ የሆነ መረጃ እንዲኖራቸው ስላደረጋቸው አድናቆታቸውን ችረውታል፡፡

እንደ አይ.ኢ.ኢ.አር፣ኤ.ኤል የሦስት ወር የውጤት ማሳወቂያ ከሆነ ማዕከሉ እንዲሻሻሉ ሃሳብ ከሰነዘረባቸው ነጥቦች መካከል 60 በመቶ የሚሆኑት ተቀባይነትን አግኝተው በመጨረሻው ሕግ ላይ ተካተዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ማዕከሉ የሀገሪቱ ብሔራዊ አየር መንገድ የሆነው ኤሮላይንስ አርጀንቲና የሚመራበት የሕግ ማዕቀፍና ይኸንኑ አየር መንገድ ወደ ግል ይዞታ ከማዞር ጋር የተያያዙት ሕጐች ላይ ኃሳብ አቅርቧል፡፡ በዚሁ በሪፖርቱ በተሰነዘረው ኃሳብ የተወሰኑ የግል ድርጅቶች ይሄንኑ ድርጅት ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር ፍትሃዊ የሆነ ውድድር እንዳይካሄድ ማድረጋቸውን ጠቁሟል፡፡ የሀገሪቱ ኮንግረስ ማዕከሉ ካቀረባቸው ውስጥ አንዱን በመቀበልም የልዩ በረራዎችን ሕግ እንደገና አሻሽሏል፡፡

## ፔሩ

አንዳንድ ወቅታዊ ክንውኖች የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማሻሻያ እድሎችን መስኮቶች ለመክፈት ችለዋል፡፡ በሀገሪቱ የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ አመፅ እና የሙስና ቅሌት የሀገሪቱ መሪ የሆኑት ፉጂሙሪ ሥልናቸውን እንዲለቁ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም የተነሣ አዲሱ ፕሬዚዳንትና የመማክርት ጉባኤያቸው በአውሮፓውያኑ የጊዜ ቀመር በ2001 መጀመሪያ ላይ ተመርጠዋል፡፡ እ.ኤ.አ ከጁላይ 2000 ጀምሮ በሀገሪቱ ተንሠራፍቶ በነበረው አደገኛ ሙስና የተነሳ ፔሩአውያን ለውጥ ይፈልጉ ነበር፡፡

የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ራሳቸውን ከፉጂሙሪ ዘመን ፖለቲካ ለማራቅ በሚል የገበያ ሥራዓቱ ማሻሻያ እንዲገለበጥ ጥሪ ያቀርቡ ነበር፡፡ ይህ በመሆኑም ኤፒኦዋይኦ የተሰኘው ተቋም ይሄንኑ አጋጣሚ በመጠቀም በዚሁ ፖለቲከኞች አዲስ ሃሳብ በሚቀበሉበት የ2001 ምርጫ ከተካሄደ በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ተከታታይ ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉ በሕዝቡ ውስጥ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ያከናወነ ሲሆን፣ የሕግ ማማከር ፕሮግራም እንዲጀመርም አበራቷል፡፡

ይህ ፕሮጀክት በጉባኤው ፣ በኤክስፐርቶችና በሲቪል ሶሶይቲ መካከል ጠንካራ ግንኙነትን በመመሥረት ዲሞክራሲን በማጐልበት ላይ እና ጉባኤው በመረጃ ላይ የተደገፈ ውሳኔ በመስጠት ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ እንዲሆን እና ተሀድሶን የሚደግፍ የኢኮኖሚ ማዕቀፍ እንዲኖረው በማስቻል ላይ ተመስርቶ የታቀደ ነው፡፡

በዚህ ፕሮጀክት አማካኝነት የምጣኔ ኃብት ባለሙያዎችና የሕግ ባለሙያዎች ቡድን ኤፒኦዋይኦ የተሰኘውን ተሀድሶ ለማምጣት ቁልፍ የሆኑ ርዕሶችን በማመላከት አጠቃላይ የሆነ ገበያ መር የኢኮኖሚ ማዕቀፍ የሚያዘጋጀውን ተቋም መስርተዋል፡፡ ከዚህ እነርሱ ወሳኝ ናቸው ብለው ከሚያዘጋጁዋቸው ዝርዝሮች ውስጥ አዲሶቹ የፓርላማ ተመራጮች አምስት ርዕሶችን ይመርጣሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ኤፒኦዋይኦ ለእያንዳንዱ ለተመረጠው ርዕስ አንድ መረጃ የሚሰጥ የዜና መጽሔት ያዘጋጃል፡፡ እያንዳንዱ መጽሔት ጥልቀት ያለው ምርምር፣ ከግሉ ዘርፍ መሪዎችና ከባለሙያዎች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስና ምክክርን የያዘ አጭርና ተጨባጭ መረጃን የሚሰጥ ነው፡፡ መጽሔቱ ለፕሮጀክቱ በተዘጋጀው ድረ ገጽ እና በኢሜል ጭምር የሚሠራጭ ሲሆን፣ አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የኢሜል ዝርዝር ውስጥ ለተካተቱት ወገኖች በኢሜል በመላክ እና አትሞ በማውጣትም ለጉባኤው አባላትና ለሲቪል ሶሶይቲ አባላት ተሰራጭቷል፡፡

ይሄው ኢሜልና ድረ ገጹ በኤፒኦዋይኦ ባልደረቦች ፣ በፓርላማ አባላትና በሲቪል ሶሳይቲ አባላት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖር ከማስቻሉም በተጨማሪ እያንዳንዱ ወገን

ፕሮጀክቱን አስመልክቶ ያሉ መረጃዎች ሁሉ እንዲደርሱትና እነዚህንም በማጤን የኢኮኖሚ ማሻሻያ የሚወሰድባቸውን ጉዳዮች አስመልክቶ ያለውን አስተያየት እንዲሰጥ ይረዳል፡፡

ኤፒኦዋይኦ የትንታኔውን ቅጂ አትሞ በማዘጋጀት ለፓርላማ አባላት፣ ለንግዱ ኅብረተሰብ፣ ለመገናኛ ብዙሃን፣ ለትምህርት ተቋማትና ለሲቪል ማኅበረሰብ አባላት ያሠራጫል፡፡ ልዩ ሴሚናር በማዘጋጀትም እያንዳንዱ የተዘጋጀው መጽሄት ላይ ለፓርላማ አባላት፣ ለንግዱ ኅብረተሰብ መሪዎችና ለፖሊሲ ኤክስፐርቶች ገለጻ ይደረጋል፡፡ ሴሚናሩ በእያንዳንዱ ውስን ጉዳይ ላይ ፓርላማዊ የሆነ አስተያየት ወይንም ምላሽን በማግኘት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በሴሚናሩ ላይ የሚደረገው ውይይት እያንዳንዱ የፓርላማ አባል ፖሊሲን አስመልክቶ ያለውን አቋም የሚያሳይ ከመሆኑም በተጨማሪ ኤፒኦዋይኦ የሕግ ለውጥን ከማምጣት አንጻር በቂ ፖለቲካዊ ድጋፍን ለማግኘት ለሚነድፈው እቅድ መሠረት የሚያስጥለውም ነው፡፡

በተለያየ ጊዜ በኒካራጓ የሚገኘውን የንግድ ድርጅቶች ከፍተኛ ካውንስልን፣ የፖላንድ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤትን እና የቦሊቪያ የግል ነጋዴዎች ኮንፌዴሬሽንን ጨምሮ በርካታ የንግድ ማኅበራት ተመሣሣይ ፕሮግራሞችን አካሂደዋል፡፡

ለምሳሌ በሕንድ ተመሣሣይ የኢኮኖማ ፖሊሲ ለውጥ ተካሂዷል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ

የመንግሥት ባለሥልጣናት ይኸንኑ ጉዳይ አስመልክቶ ያሏቸውን መሠረታዊ ተቃዋሚዎቻቸውን ከማስወገዳቸው በፊት የሚደረገው ማሻሻያ የአካባቢያቸውን ኅብረተሰብ በትክክል ይጠቅም እንደሆነ ማሳመን ይፈልጉ ነበር፡፡ ኒውደልሂ የሚገኘው የዘርፍ ንግድ ምክር ቤት በብሔራዊ ደረጃ ያሉ የመንግሥት ባለሥልጣናትን፣ ታዋቂ የንግድ ሰዎችንና የትምህርት ተቋማትን ለማግኘት በመላው ሰሜን ህንድ 31 የሚደርስ የነጋዴ እና የመንግሥት የምክክር መድረኮችን አዘጋጅቷል ፡፡ ይህ መድረክ የተካሄደው፡፡

- በመንግሥት ባለሥልጣናት አስተሳሰብ ውስጥ «አይቻልም» የሚለውን አስወጥቶ «ይቻላል» የሚለውን ለማስቀመጥ፣
- ከህንድ ፖለቲካ ውስጥ «ፀረ-ትርፍ» አስተሳሰብን ለማስወገድ እና
- ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፈቃድና ማስረጃን ሳይንከራተቱ ማግኘት ለማስቻል ነበር፡፡

ምንም እንኳን አስተሳሰብንና አመለካከትን የመቀየር ተግባር ረጅም ጊዜን የሚፈልግ ቢሆንም፣ የደልሂ ንግድ ምክር ቤት ግን በርካታ ውጤቶችን መጨበጡን አስታውቋል፡፡